

አቤቱ አምላካችን ሆይ ለቅዱስ ስምህ ቤት እንሠራ ዘንድ ይህ ያዘጋጀነው ባለጠግነት ሁሉ ከእጅህ የመጣ ነው ፤ ሁሉም የአንተ ነው ።

# ትንሣኤ



አምላክ ሆይ በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነው ባለጠግነትና ክብር ከአንተ ዘንድ ነው ሁሉ ከአንተ ዘንድ ነው ። .... ከእጅህም የተቀበልነውን ሰጥተንሃል ። (1 ዜና 29፡11)

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር 38. ኅዳር ፲፱፻፹፫

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት ፀተግባር ጭምር እንዲተረ ጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።


አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


## ማሳሰቢያ

በትንሣኤ መጽሔት ቁ/37 ላይ ስለ አባ በላይ ወጥቶ የነበረው ጽሑፍ ያልደረሳቸው አንባብያን በድጋሚ ተባዝቶ እንዲደርሳቸው በስልክና በደብዳቤ በብዛት ስለጠየቁን በዚህ እትም በድጋሚ አውጥተነዋል ።

## ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | 1 |
| የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር | 2 |
| ከመላእክት አንዱ ሚካኤል | 3 |
| የሃያኛው ክፍለ ዘመን ብቃት | 4 |
| ከአሥር አንድ ለእግዚአብሔር (ዓሥራት) | 8 |
| የሴቶች ዓምድ | 10 |
| ለጥምቀት የሚያስፈልጉ ሦስት ዋና ዋና ነገሮች | 13 |
| ይህን ያውቁ ኖሯል? | 14 |
| ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ | 15 |
| ቤተ ክርስቲያን በኅብረተሰብእ | 16 |
| ጽዮን ታቦተ ሕግ ወኪዳን | 17 |
| ሊቃውንቶቻችን | 18 |
| በኤርትራ ሀገረ ስብከት የሰበካ ጉባኤ አቋም | 20 |
| ወጣቶች በመንፈሳዊ ሕይወት | 22 |
| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር | 24 |


## ደብዳቤዎች

ለትንሳኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከሁሉ አስቀድሜ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም የማክበር ሰላምታዬን እያቀረብኩ የሚከተለውን ጥያቄ አቀርባለሁ ። ባለፈው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል የዋለው ሰኞ ነበር ማለትም በ28/4/72 ዓ.ም ሲውል አንዳንዱ የገሃድ ጾም ቅዳሜና እሁድ ነው ሲል አንዳንዱ ደግሞ እሁድ ብቻ ነው ቅዳሜ ይበላል ብሏል ስለዚህ ትክክለኛው የቱ እንደሆነ እንድትገልፁልኝ እጠይቃለሁ ።

የመጽሔታችሁ ተከታታይ
ተማሪ ደረጀ አክሊሉ
የቅድስት ልደታ የወጣቶች መንፈሳዊ ማህበር አባል አዲስ አበባ
የፖ.ሣ. ቁ.183

----የልደትም ሆነ የጥምቀት በዓላት ሰኞ ቢውሉ የገሃድ ጾም እሑድ ብቻ ነው እንጂ ከቅዳሜ 4 ሰዓታት ከእሑድም 3 ሰዓታት አውጣጥቶ አንድ የገሃድ ቀን መፍጠር በጥንታዊት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አልነበረም ። የገሃዱም ጾም ዓላማ በማግሥቱ የሚከበረውን በዓለ ልደት በመንፈሳዊ ዝግጅት ለመቀበል ስለሆነ አኃት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በዋዜማው ዕለት ብቻ ገሃድን ይጾማሉ ። ግን ሁለቱም ቀናት ገሃድ ነው የሚሉ ሰዎች በእሑድ ቀን ጾም እንደሌለ በማሰብ ነው ። እዎ በእሑድም ቢሆን ከጥሉላትና በቅዱሳት መጻሕፍት ከተጠቀሱት መጥፎ ድርጊቶች መከልከል ይገባል ሌሎችም የስንክሳር መጽሐፍ ልደት ሰኞ ቢውል ገሃድ እሑድና ቅዳሜ እንዲጾም ያዝዛል ይላሉ ። ይሁን እንጂ በዚህ አሳብ ሁሉ አይስማማበትም ።

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ጥያቄዎች አሉኝ፡-
ከሁሉ አስቀድሜ መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ። የትንሣኤን መጽሔት ሳነብ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው ብዬ ብናገር ስነፍ ወይም ዝንጉ ሳይሉኝ ግንቦት 1972 ዓ.ም በቁጥር 32 የወጣውን አንብቤ ያገኘሁትን ጥያቄዎች በጥሞና ተመልክተው መልስ እንዲሰጡኝ በትሕትና እጠይቃለሁ ።

1. ስለ ሊቁ ፊላታዎስ

እኚህ ሊቅ ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ውለታ የዋሉና ቅርስ ያስቀሩልን መሆናቸው ተጠቅሷል ። እኔ የርሳቸውን የሕይወት ታሪክ ሳነብ የመጀመሪያ ጊዜዬ ስለሆነ ፡-

ሀ-ስለ ሊቁ ፊላታዎስ ሕይወት ታሪክ በዚህ መጽሔት ሰፋ አድርገው ቢያወጡ ወይም ተጽፎ ካለበት ቢጠቁሙኝ ፡-

ለ- በብርቱ ሁኔታ ያሰቃያቸው የነበረ ደዌ እንደነበረባቸው ተጠቅሶአል ፤ ምን ዓይነት ደዌ እንደነበር ቢገለጽ፡-

2. ስለ ባለዜማው ያሬድ

ሀ- የታወቀው ባለዜማው ያሬድ "ከቤተ ነፋስ ወገን ተወለደ" የሚባለው ቤተ ነፋስ የተባለው ወገን እንዴት እንደሆነ ቢገልጹልኝ፡-

ለ- የታወቀው ባለዜማው ያሬድ የተወለደበት ቦታና ወገን ተገልጾአል የተወለደበት ጊዜም ቢገለጽ በጣም ደስ ያሰኛል ።

ሐ- ቅዱስ ያሬድ የሞተበት ጊዜ ግንቦት 11 ቀን ከሆነ ዓ.ም መቼ ነው?

3. ስለ ደብረ ሊባኖስ ገዳም

ሀ- ገዳሙ በስማቸው የተጠራው መናኝ መነኩሴ አባ ሊባኖስ የተባሉት ስሙ የግሪክ ስም ይመስላል ፤ ምናልባት መቼ ከየት እንደመጡ ቢታወቅ ይገለጽ አደራ?

ለ- በደብረ ሊባኖስ ገዳም የሚካሄደው የአገልግሎት ተራ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከዓመቱ መጀመሪያ ሳይሆን ከሰኔ ወር የሚጀምር መሆኑ ተገልጾአል ። ይህ ሁኔታ ሌላ የሚጠቁም ታሪክ አለው ወይስ በልማድ የተደረገ ነው? ተራው በዚህ ዓይነት መሆኑ የጥንት ነው ወይስ በጊዜ ብዛት የተሻሻለ ነው?

4- ስለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፡-

የተወለዱበት ጊዜ መገለጹ በእውነት የአንዱን ሰው የሕይወት ታሪክ ተጨባጭ ከሚያደርጉት አንዱ ነገር ታወቀ ማለት ነው ።

ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከዚህ ዓለም መለየታቸው ዓመተ ምህረቱ ሳይቀር ሲገለጽ የተቀበሩበት ቦታ ደብረ አሰቦ ተብሎአል ። እንደኔ ቦታዎችን በብዛት ለማያውቁ ችግር እንዳይፈጥር እስከ ክፍለ ሀገሩ ቢገለጽ?

አስተያየት

ይህን መጽሔት ሳነብ የመጀመሪያ ጊዜዬ መሆኑን ቀደም ብዬ የገለጽኩ ሲሆን ከዝግጅቱም ያነበብኩት ይህ የመጀመሪያ ጽሑፍ መሆኑ ነው ። ቤተ ክርስቲያኒቱ በዚህ ዝግጅት አማካይነት ስለምትሰጠው ትምህርትና ሰላምታ ስለተላለፈው መልእክት እጅግ ደስ የተሰኘሁ መሆኔን ስገልጽ ፤ በተለይ "ምን እንርዳዎ" የተሰኘው ርእስ ከፍተኛ መሆኑን ሳረጋግጥ ታላቅ ደስታ እየተሰማኝ ነው ።

እግዚአብሔር የዚህን መጽሔት አገልግሎት ይባርክ አሜን"

ቄስ ለሜሳ በቶ

- ቄስ ለሜሳ በቶ ስለ ጥያቄዎችዎና አስተያየትዎ እጅግ እናመሰግናለን ።ስለሊቁ ፊላታዎስ የህይወት ታሪክ ምንጭ ያገኘን ከደቀ መዝሙራቸው ከመምህር ጌራ ወርቅ ነው ። እርሳቸውም የሚገኙ በበዓታ ገዳም መንፈሳዊ ት/ቤት ስለሆነ ቢጠየቁ በሰፊው ማስረዳት ይችላሉ ።

2. ባለዜማው ያሬድ "ከቤተ ነፋስ" ወገን ነበር ማለት ፡- በአክሱም አካባቢ ቤተ በግዖ ቤተ ነፋስ ወዘተ በመባል የሚጠሩ ሰባት አቅኝዎች ነበሩ ።እንግዲህ ያሬድ ከሰባቱ የአንደኛው ቤተ ነፋስ ከተባለው አቅኚ ወገን ነበር ያሬድ በ505 ዓ.ም ተወልዶ በ651 ዓ.ም ሞቷል ።

3. (ሀ) አባ ሊባኖስ የተባሉት መነኩ

ወደ ገጽ ፮ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ርእስ አንቀጽ

# የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር

ስጦታ የፍቅር መግለጫ ነው ፣ እግዚአብሔር ፍጥረቱን ይወዳል ፣ በተለይ በሰው ልጅ ላይ ያለው ፍቅር ፍጹም ነው ። ስለሆነም የሚያስፈልገውን ሁሉ ሰጥቶታል ይሰጠውማል ። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የለገሰው ስጦታ ብዙ ነው እግዚአብሔር ያደረገውን ያህል ሰዎች ለእርሱ ሊያደርጉለት አይችሉም ።

ግን ሰዎች በእዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ለመግለጽ እግዚአብሔር ከሰጣቸው ከብዙው ነገር ጥቂት (ከአሥር አንድ) እንዲሰጡ ተጽፎአል ዘሌዋ. 27:30 በየብስና በባሕር በዕፀዋትና በእንስሳት የሚገኘውና ለሰዎች ጥቅም የሚሆነው ከእግዚአብሔር ለሰዎች የተሰጠ ነው ። ስለዚህ ብዙ ተቀብለን ጥቂት ብንሰጥ ሌላ ተጨማሪ በረከት ይታዘዝልናል ። ምእመናን ለእግዚአብሔር ቤት ከአሥር አንድ ወይም ከዚያ የበለጠ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ በብሉይ ኪዳን ተደጋግሞ ተገልጦአል ።

ምእመናን አሥራት እንዲሰጡ የሚጠየቁት ለምን ነው? እግዚአብሔር አንድ ልጁን ለእነርሱ ቤዛ አድርጎ ለሞት አሳልፎ እስከ መስጠት ስለወደዳቸውና መድኀን ክርስቶስም ራሱን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ሕይወቱን እስከ መስጠት ስለ አፈቀራቸው ነው ። ለወደዳቸው ለእግዚአብሔር በደስታ መስጠት እንደሚገባ መጻሕፍት ያስረዳሉ "እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም" 2ቆሮ 9 ፣ 7 " የሚሰጥ በልግስና ይስጥ" ሮሜ 12፥8 "እምላክህ እግዚአብሔር በረከት እንደሰጠህ መጠን እያንዳንዱ ሰው እንደ ችሎታው ይስጥ" ዘዳግ 16 ፣ 17 ።

አዎ ምእመናን ለእግዚአብሔር የሚሰጡት በደስታ እንጂ በኀዘን መሆን የለበትም ፣ የሚችሉትን እንጂ የማይችሉትን አይደለም በውድ እንጂ በግድ አይደለም ፣ በየሳምንቱ እሁድ በእግዚአብሔር ቤት እየተገኘን የእግዚአብሔርን ቃል መስማት መንፈሳዊ ግዴታችን ነው እንዲሁም ለእግዚአብሔር ቤት አገልጋዮችና ለድሆች መርጃ የገንዘብ አስተዋጽኦ (አሥራት) ይፈለግብናል ።

የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ማለትም እርሱ ከሰጠን ከብዙው ጥቂት (ከአሥር አንድ) ባንሰጥ እንደ ሰረቅን ይቆጠራል "ሰው እግዚአብሔርን ይሠርቃል? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል እናንተም የሠረቅንህ ምንድን ነው? ብላችኋል በአሥራትና በበኩራት ነው "ሚል 3 ፣ 8 ጥቂት ሰጥተን ብዙ በረከትን እንቀበላለን "በቤት ውስጥ መብል እንዲሆን አሥራቱን ሁሉ ወደ ጐተራ አግቡ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ" ሚል 3 ፣10 "ስጡ ይሰጣችኋል በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋል" ሉቃ. 6፥38 "መስጠት ቤት አይፈታም" የሚል የአበው አነጋገር አለ መጻሕፍትም መስጠት በበረከት ላይ በረከትን እንደሚሰጥ ያስረዳሉ መስጠት ጉድለትን አያመጣም አለመስጠት ግን እንደ ስርቆት ይቆጠራል ስርቆትም ያስቀጣል ። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ሰጥቶ መንፈሳዊ በረከትን መቀበል ፣ በእምነትዋና በሥርዓትዋ ሥር ያሉባትን ቤተ ክርስቲያን መርዳትና መንፈሳዊ አቅዋምዋ እንዲጠናከር ማድረግ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም ነው ። በተግባርም ማለት በቃላችን እየመሰከርንና እምልኮታችንን እየገለጥን ከምናገኘው ሀብት ሁሉ ከዐሥር አንድ ወይም የተቻለንን የፈቃድ ስጦታ መስጠት ነው ።

# ከመላእክት አንዱ ቅዱስ ሚካኤል

ሚካኤል ማለት በዕብራይስጥ ቋንቋ "ማን ነው እንደ አምላክ"ን ማለት ነው። ሚ ማን ነው? ካ እንደ ኤል አምላክ ማለትን ያስተረጉማል ሚካኤል የሚለው ስም በብሉይ ኪዳን ውስጥ 13 ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል ከእነዚህም መካከል አሥሩ የተለያዩ ሰዎች የተጠሩባቸው ሲሆኑ ሦስቱ ታላቁ አለቃ ወይም ሊቀ መላእክት ሚካኤልን ያመለክታሉ ።ሚካኤል በስም ተለይተው ከሚታወቁት መላእክት አንዱ ነው በተለይም የእስራኤላውያን ጠባቂ መልአክ እየተባለ ይጠራል ። ይሁን እንጂ በእምስቱ መጻሕፍተ ሙሴ ውስጥ ሚካኤል በስም ተገልጦ አልተጠቀሰም ብቻ የእግዚአብሔር መልአክ ፣ አንዳንድ ጊዜም መልአክ ገጽ በመባል ተጠቅሶአል ሚካኤል በስም ተለይቶ መጠቀስ የተጀመረው በመጽሐፈ ዳንኤል ነው (ዳን 10 ፣ 13 እና 21 ። 12 ፣ 1) እርግጥ በመጽሐፈ ሄኖክ ብዙ ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል ።ከዚህም ሌላ በብሉይ ኪዳን አዋልድ ለምሳሌ በኪዳነ ሌዊ (5፥6) በኪዳነ አብርሃም 11 ተጠቅሶአል ።

ቅዱስ ሚካኤል በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ብዙ ሥራዎችን ሠርቶአል ።

1- የእግዚአብሔር ሕዝብ እስራኤላውያን በግብፅ ለብዙ ዓመታት በባርነት ከኖሩ በኋላ በልዩ ልዩ ተአምራት እንዲወጡ ቅዱስ ሚካኤል ከእግዚአብሔር እየተላከ ረድቶአቸዋል ። በመጨረሻም ባሕረ ኤርትራን ሲሻገሩ ስለባሕሩ መከፈል የእግዚአብሔር መልአክ የቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት እንደነበረበት ቅዱስ መጽሐፍ በሰፊው ያስረዳል (ዘጸአት 14 እና 15)

2- ቅዱስ ሚካኤል በእግዚአብሔር ፊት ለእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚማልድና ምሕረት የሚለምን መልአክ ነው፣ ኪዳነ ዳን . 6 ፣2 ። በዕርገተ ኢሳይያስ 9 ፣ 23 ላይ እንደተገለጠው ቅዱስ ሚካኤል ቅዱሳንን በችግራቸው ጊዜ ይረዳል ። ጸሎታቸውን ወደ እግዚአብሔር ያቀርባል ለኃጢአተኞች የኃጢአት ሥርየትን ለማሰጠት ይተጋል ።

3- ለእስራኤል የሚቆምላቸው ጠበቃ ጠላቶቻቸውን ድል የሚያደርግ ኃይል ነው ። ዳን. 12 ፣1 ።

4- ሰዎችን ሁሉ በማንኛውም ሥጋዊና መንፈሳዊ ችግራቸው ይረዳል ፣ዳን 10፥13 ።ከኃዘናቸው ያጽናናል ዳን.10፥21 ።

5- በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ የሚነሱ ጠላቶችን ይቃወማል ይገሥጻልም ፣ እነዚህም የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች የሚባሉ ሰይጣናት ናቸው (ራእ . 12፥7 ይሁዳ 9)

6- ሙሴ በደብረ ሲና ሕግን ከእግዚአብሔር በተቀበለ ጊዜ ቅዱስ ሚካኤል በእግዚአብሔርና በሙሴ መካከል አገልጋይ እንደ ነበረ በመጽሐፈ ኩፋሌ 2፥1 ላይና በዕርገተ ኢሳይያስ 11፥21 ላይ ተገልጦአል ። ከዚህም ሌላ ሊቀ መላእክት ሚካኤል በእግዚአብሔር ዙፋን ከሚቆሙ ጌታን ከሚያገለግሉ መላእክት አንዱ መሆን በመጽሐፈ ሄኖክ 10፥5 ላይ ተጠቅሶ ይገኛል ። በዚህም ጥቅስ መሠረት በእግዚአብሔር ፊት ከሚቆመው ከገብኤል ጋር አንድ አይነት ባለሟልነት እንዳለው እንረዳለን ።

በመካከለኛው የክርስቲያኖች ዘመን ዐርት (ሥዕል) ቅዱስ ገብርኤልና ቅዱስ ሚካኤል በእመቤታችን ድንግል ማርያም በቀኝና በግራ በኩል ቆመው መሣል ተጀምሮአል ። የሥዕሉም ሁኔታ እንደሚከተለው ነው 1ኛ/ ሁለቱም መላእክት ሰይፍ ወይም ሰይፍና አበባ እንዶ ያዙ ይሣላሉ ፣ 2ኛ/ ገብርኤል መስቀል ሲይዝ ሚካኤል ጦርና ሰፈነግ ይዞ ይሣላል ። በቅዱሳት መጻሕፍትና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስለ ቅዱስ ሚካኤል ከተጻፈው ተመልክተናል ።በተለይም ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሚካኤል ታላቅ ክብር ያለው በአማላጅነቱና በታዳጊነቱ የሚታመንበት መልአክ እንደመሆኑ መጠን በየወሩ በ12ኛው ቀን በታላቅ መንፈሳዊ ሥርዓት ይከበራል ።ይህም በ13ኛው ምእት ዓመት እንደ ተጀመረ የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ያስረዳል ። ይልቁንም ኅዳር 12 በሚካኤል ስም በታነጹ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ከፍተኛ ክብረ በዓል ይደረጋል ።ይህም እስራኤልን ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ ያሻገረበትን ለማስታወስ ነው ።ይህ ብቻ ሳይሆን አማላጅነቱንና ለሰው ልጆች የሚያደርገውን ተራድኦ ሁሉ በማመን እግዚአብሔር በቅዱሳን መላእክቱ በኩል የሚሰጠውን ጸጋ ለመቀበል እናከብረዋለን ። እነዚያን የእግዚአብሔር ሰዎች ባሕር ከፍሎ እንዳሻገራቸው ዛሬም በእግዚአብሔር የሚያምኑ ወገኖችን ሁሉ ከልዩ ልዩ መከራና ፈተና ያወጣቸዋል ። በጠላቶቻቸው በሰይጣናት ፊት እንደ ጠበቃ ይቆምላቸዋል በመንፈሳዊ ፍላጎታቸው ሁሉ ይረዳቸዋል ። ከኃዘናቸውም ያጽናናቸዋል በጠቅላላ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም ፍጹም ባለሟልነት ስላለው በእግዚአብሔር ለሚያምኑ ሁሉ ምሕረት ለማኘና አጽናኝ (ሰአሌ ምሕረት) በመሆኑ እናከብረዋለን ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

# የሐያኛው ክፍለ ዘመን ብቃት

በሃይማኖት ዓለም ውስጥ ሰዎች ወደፍጹምነት ደረጃ ሲደርሱ እንደሚሰወሩ የሃይማኖት መጻሕፍት ይናገራሉ። መሰወር ማለትም በዋሻ ውስጥ መደበቅ ከሰዎች ተለይቶ መራቅ በጫካ መከለል በገደል መጠለል አይደለም። ግን ከሰዎች ጋር እያሉ ለሰዎች አለመታየት ማለት ነው። ሆኖም በምትሐት ሳይሆን ከፍጹም እምነት የተነሣ በምግባርና በትሩፋት ከእግዚአብሔር በሚሰጥ መንፈሳዊ ጸጋ ነው። ለምሳሌ ሄኖክና ኤልያስ ሳይሞቱ በሕይወት ተሰውረው እግዚአብሔር በፈቀደላቸው ቦታ እንደሚኖሩ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል (ዘፍጥ 5፡21-24። 2ነገሥ. 2፡1-11) ነቢዩ ኤልሳዕ ለሌሎች የማይታዩ የተሰወሩ ሠራዊትን ያይ ነበር (2ነገሥ6፡14-18) ቅዱስ ጳውሎስም በሕይወቱ ወደ ገነት ወይም እስከ 3ኛ ሰማይ ድረስ እንደተወሰደና በዚያም ሰው ሊናገረው የማይገባውን ቃል ሰምቶ እንደተመለሰ ይናገራል (2 ቆሮ 12፡2-5)። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ሰዎች ሲበቁ ወይም በእምነትበምግባርና በትሩፋት ፍጹማን ሲሆኑ ከእግዚአብሔር የሚሰጣቸውን ጸጋ ነው።

ከዚህም ሌላ በዘመናችን አንዳንድ ሰዎች ዓይን በዓይን ከሰዎች ፊት እንደ ተሰወሩ ሳንሰማ አልቀረንም ለምሳሌ ከ8ዓመታት በፊት በሐረርጌ ክፍለ ሀገር በሐረርከተማ 4 ሰዎች በፍርድ ሸንጎ ቆመው ሳሉ ከተሠየሙት ዳኞችና በፍርድ ሸንጎው ዙሪያ ከነበሩት ሰዎች መካከል ተሰውረዋል። ይህም ዜና በጊዜው በዓይን ምስክሮች አቅራቢነት በጋዜጦች ወጥቶአል በሬድዮም ተነግሮአል። ይህ አይነቱ መሰወር የሰውን ልጅ ረቂቅ ጥበብ ያመለክታል።

በዓለም ውስጥ አልፎ አልፎ ለሰዎች የማይታዩ ልዩ ፍጡራን እየተከሠቱ የሰው ልጆችን ነጥቀው እንደሚወስዱ ከጥቂት ቀናት በኋላም እንደሚመልሷቸው ተወስደው የተመለሱት ሰዎች ራሳቸው አውርተዋል። እነዚህ ሰዎች የማይታዩ ልዩ ፍጡራን ፍላይንግ ሶሰርስ ተብለዋል በእኛም ቋንቋ ጁደነት ልንላቸው እንችላለን። እነዚህ ልዩ ፍጡራን በድንገት እየተከሠቱ አንዳንድ ሀገሮችን እንደወጉ ይነገራል።

ይህን ሁኔታ ስንመለከት የእግዚአብሔር ፍጥረት ብዙና ረቂቅ ግሩምና ድንቅ ከመሆኑም በላይ በሰዎች አእምሮ ገና ያልተደረሰበት ሊደረስበትም የማይቻል መሆኑን እንረዳለን።

አሁን በዚህ ጽሑፍ ከብዙ ዘመናት በፊት ስለተሰወሩ ሰዎችና ስለ ልዩ ልዩ ፍጡራን በሰፊው አንተርክም፤ በዚህ ጽሑፍ ልንገልጥ የፈለግነው በጊዜያችን ከሁለት ወራት በፊት ስለተሰወሩት አባ በላይ ወ/ሚካኤል ስለተባሉት መነኩሴ ነው። አባ በላይ በ1887 ዓ.ም. በኤሉባቡር ክ/ሀገር ተወለዱ። በጠላት ጊዜ ከትውልድ ሀገራቸው ወጥተው ለአምስት ዓመታት በአርበኝነት ቆይተዋል



የተሰወሩት አባ በላይ እኒህ ናቸው።

ጠላት ከኢትዮጵያ ከወጣ በኋላም ወደ አዲስ አበባ መጥተው ለአንድ የግል ድርጅት በአሠሪነት ተቀጥረው ለብዙ ዓመታት ሠርተዋል። ከዚያም ከአዲስ አበባ ወደ ሐረርጌ ክፍለ ሀገር ተዛውረው በሚኤሶ ከተማ ውስጥ በአንድ ሆቴል ቤት ኀላፊ ሆነው ከ54 እስከ 67 ዓ.ም. በቅንነት ሲያገለግሉ ይቆያሉ። በአንድ ሌሊትም በሆቴሉ ውስጥ በተሰጣቸው መኖሪያ ክፍል ውስጥ ተኝተው እንዳሉ የብርሃን ልብስ የለበሰች የወርቅ መስቀልና ጃንጥላ የያዘች እንደ ፀሐይ የምታበራ አንዲት ሴት "በዚህ ቦታ ምን ታደርጋለህ? ከዛሬ ጀምሮ ወደ እኔ ና" ብላ በራእይ ትነግራቸዋለች። ሲነቁ ተገረሙና "ምን ይሆን ? በማለት የተነገራቸውን ትእዛዝ በሥራ ላይ ሳያውሉ የተለመደ ሥራቸውን ይከታተላሉ።

2ኛ በሌላ ጊዜ እንደቀድሞው አንዲት ሴት በተመሳሳይ ሁኔታ በራእይ ተገልጣ "ገዚህ ቦታ ውጣና ወደ እኔ ና አላልሁህምን" በማለት ስትቆጣቸው ደንግጠው "ወዴት ነው የምሄደው ? ሲሉ "ወደ መቃብር ቤት ግባና ተቀመጥ" አለችኝ በማለት አባ በላይ ለቅርብ ወዳጆቻቸው ተናግረዋል። በተደጋጋሚ በራእይ የታየቻቸው ሴት እመቤታችን ቅ/ ድንግል ማርያም እንደ ሆነች በመረዳት በማግሥቱ ጥዋት ተነሥተው ወደሚኤሶ ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ገብተው በመቃብር ቤት ይቀመጣሉ፤ በዚያም በዕቅብና እያገለገሉ ቆይተው በ1971 ዓ.ም. በግንቦት ወር መጨረሻ አባ መዘምር አፈወርቅ ከተባሉ መነኩሴ የምንኩስና መዐርግ ተቀብለዋል። እንደገናም በሚኤሶ ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን የዕቅብና ሥራቸውን ቀጥለው እስከ ሰኔ ወር 1972 ዓ.ም. ይቆያሉ።

3ኛ ጊዜ በሰኔ ወር 1972 ዓ.ም. እመቤታችን በራእይ ተገልጣ "ክፍልህ አሰቦት ገዳም ነው ወደዚያ ሂድ" ትላቸዋለች። አሰቦት ገዳም በሐረርጌ ክፍለ ሀገር በጨርጨር አዳልና ጋራ ጉራቻ አውራጃ የሚገኝ ገዳም ነው። የተመሠረተም በ12ኛው ምእት ዓመት በጻድቁ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዝሙር በአባ ሳሙኤል ነው። ገዳሙ የተመሠረተው በከፍተኛ ተራራ ላይ ነው። ከአሰቦት ባቡር ጣቢያ እስከ አሰቦት ገዳም 20 ኪሎ ሜትር ይሆናል።

አባ በላይ ወደ አሰቦት ገዳም እንዲሄዱ በራእይ በተነገራቸው ትእዛዝ መሠረት ሰኔ 28 ቀን 1972 ዓ.ም. ወደ ገዳሙ ይሄዳሉ፤ በዚያም እስከ ሐምሌ 6 ቀን 72 ዓ.ም. በአባ ጌዴዎን ቤት ይቀመጣሉ። ሐምሌ 6 ለ7 አጥቢያ በመንፈቀ ሌሊት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የብርሃን ልብስ ለብሳ ለ4ኛ ጊዜ ተገልጣ፤

"ሐምሌ 7 ቀን 72 ዓ.ም. ሥጋ ወደሙን ተቀበል፤ ከዚያም በኋላ እህልና ውሃ አትቅመስ፤ ከዑደት (ታቦት ከዞረ) በኋላ የሚያነጋግርህ ሰው ይመጣል አትደንግጥ አትፍራ አትጠራጠር ለአንተ የሚታይህ ለሌላው አይታይም ለአንተ የሚሰማህ ለሌላው አይሰማም የሚነግርህን ስማ" አለችኝ በማለትያዩትን ራእይ ለአባ ጌዴዎንና ለአባ አምሐ መኰንን ተናግረዋል። አባ በላይ ይህን ራእይ በማየታቸው ከዚህ ዓለም በሞት የሚለዩ ስለመሰላቸው ሐምሌ 7 ቀን 72 ዓ.ም. ሌሊቱን በሙሉ ሲንቀጠቀጡ ሲጸልዩና ሲያለቅሱ ማደራቸውን አባ ጌዴዎን ገ/ ሚካኤል ገልጠዋል።

ሐምሌ 7 ሰኞ ጥዋት አስቀድሰው ሥጋ ወደሙን ይቀበላሉ። ከዑደተ ታቦት በኋላ ከቀኑ በ5 ሰዓት አባ በላይ አባ አምሐን ጠርተው እንዳይለዩአቸው ይነግሩአቸዋል። ሕዝቡ ከተበተነ በኋላ ከቤተ ክርስቲያኑ በስተምስራብ በጸጥታ ሁለቱ በአንድነት ይቀመጣሉ። ከዚህ በኋላ የታሪኩ ተከታታይ የነበሩት አባ አምሐ እንደሚሉት አባ በላይ በእጃቸው እያመለከቱ ጃኖ ልብስ የለበሰ አንድ ሰው በደወል መደወያው ሥር መጣ "ያለህን ዕቃ አስረክበህ ተከተለኝ እዚያ የሚጠብቁህ ሰዎች አሉ" ይለኛል በማለት ካፖርታቸውን ጋቢያቸውን ኮታቸውን ጫማቸውንና የእግር ሹራባቸውን በቆባቸው ላይ የጠመጠሙትን ሻሽ ያወልቃሉ። ጃንጥላቸውንም ያኖራሉ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ደግሞ ያ የተሰወረ ሰው ካፖርታቸውንና ጋቢያቸውን መልሰው እንዲለብሱ እንዳዘዛቸው በመናገርይለብሳሉ። ሌላውን ልብሳቸውን የስንቅ ከረጢት መሳይ ዕቃቸውን በአጠገባቸው ለነበሩ ለአባ አምሐ አስረክበዋል።



በአካባቢው የተሰወሩ ቅዱሳን አሉበት የሚባለው የአሰቦት ቅድስት ሥላሴ ገዳም

በመደነቅ ይመለከቱአቸው የነበሩት አባ አምሐ "ይህን ሰው አታየውምን? ድምፁንስ አትሰማውምን" እያሉ አባ በላይ ሲጠይቁኝ የአእምሮ ሕማም ያደረባቸው ቢመስለኝም በእርግጥ የተሰወረኝ አንድ ሰው እንደሚያነጋግራቸው ይሰማኝ ነበረ ይላሉ። ይህን አውልቅ ነው የምትለኝ ? ይህን አስረክብ ነው የምትለኝ" በማለት በተስተካከሉ ቃላት ከማልሰማውና ከማላየው ሰው ጋር አባ በላይ ሲነጋገሩና ሲታዘዙ ልብሳቸውንና ዕቃቸውንም ለእኔ ሲያስረክቡ በታላቅ ፍርሀት ተይዘው ይንቀጠቀጡ ነበር ይላሉ አባ አምሐ።

ከዚያ በኋላ አባ በላይ ለርሳቸው ብቻ የሚታየው ሰው ወደ አባ ዮሐንስ ቤት እያመለከተ "ከዚያ ቤት በስተኋላ ዋነኛው አለ እኔ መልእክተኛ ነኝና እንሂድ" ይለኛል አሉና ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አዙረው 3 ጊዜ ይሰግዳሉ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሆይ ወደ መልካም መንገድ ምሩኝ በማለት ጸለዩ በዚህ ጊዜ ዕንባቸው ፈሰሰ ወደ እኔ ዞረው አባቴ ይመለሱ ዕቃውንም ለአባ ጌዴዎን ይስጡ አቸው አሉኝና መራመድ ጀመሩ። በዚህ ጊዜ ዓይኖቼ ፈዘዙ ደነገጥሁ ተንቀጠቀጥሁ ላያቸው አልቻልሁም ከዚያ በኋላ አልተከተልሁም ወደተጠሩበት ቦታ ደርሰው ይመለሳሉ የሚል ግምት ነበረኝ ግን ሳይመለሱ ቀሩ ሲሉ አባ አምሐ መኰንን የአባ በላይን የመሰወር ዜና አስረድተዋል።


ይህ ዜና ወዲያውኑ በመነኮሳቱ ሁሉ ዘንድ ተሰማ ከዚያም አልፎ ወደ አዲስ አበባ ደረሰ እኛም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ጋዜጠኞች ይህን ዜና እንደሰማን ወደ አሰቦት ገዳም ሄደን የገዳሙን አስተዳዳሪ አባ ጥበበ ሥላሴ ታደሰን ታሪኩን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የተከታተሉ አባ አምሐ መኰንንን እስከተሰወሩበት ቀን ድረስ አባ በላይን በቤታቸው አስጠግተዋቸው የነበሩ አባ ጌዴዎን ገ/ሚካኤልን ፤ አባ ዮሐንስ አጽብሐን ዲ/ተፈራ ገ/ጻድቅን አነጋገርናል። እነርሱም ስለ አባ በላይ መሰወር ሲያስረዱ እንዲህ ብለዋል የአሰቦት ገዳም ብዙ ቅዱሳን ባሕታውያን የሚኖሩበት ገዳም ነው ብዙ የማይታዩ ቅዱሳን መነኮሳት በአካባቢው ይኖራሉ አባ በላይን የጠራቸው መልክተኛ ከእነዚያ በስውር ከሚኖሩ ባሕታውያን መካከል አንዱ እንደ



www.ethiopianorthodox.org

ሆነ እንጠራጠርም የአባ በላይም መሰ ወር በገዳሙ አካባቢ ከሚገኙ የተሰወሩ ቅዱሳን ጋር መጨመር ነው ብለን እና ምናስን ። አባ በላይ ወልደ ሚካኤል ገብተው ከነበሩት አበው መነኮሳት መካከል አንዳንዶቹ አባ በላይ ከተሰወሩ ቅዱሳን ጋር የተጨመሩ መሆናቸውን በራእይ እንደተረዱ ተናግረዋል ።

ግን ያቃወግል? ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።



የኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ ጋዜጠኛ መነኮሳቱን ስለ አባ በላይ ሲያነጋግር

የ86 ዓመት ሽማግሌ ከመሆናቸው በላይ ቅን የዋህ ትሑትና እውነተኛ አማኒ ስለነበሩ ይህ ጸጋ ሊሰጣቸው እንደሚችል የጠየቅናቸው መነኮሳት ነግረውናል ።

በተጨማሪም በጾመ ፍልሰታ ሱባኤ

አዎ "እግዚአብሔር የወደዳቸውን ይጠራል የጠራቸውንም ያከብራል" እንደተባለ አባ በላይንም በፍጹም እምነታቸውና ምግባር ትሩፋታቸው ስለወደዳቸው ሊጠራቸውና በክብርም ከቅዱሳኑ ጋር ሊያኖራቸው ከፈቀደ ፈቃዱን



አባ ዮሐንስ አጽብሐ



አባ በላይ በተሰወሩ ጊዜ የተውት ልብስ

## ደብዳቤዎች...

ከገጽ ፩ የዞረ

ሴ የመጡ ከሦርያ ሲሆን ዘመኑም በ6ኛው ምእት መጨረሻ ላይ ነበር (ሰ) በደብረ ሊባኖስ የአገልግሎት ተራ ከሰኔ ወር መጀመሩ እንደዚህ ነው ፣ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት 12 ደቀመዛሙርት በየዓመቱ በግንቦት ወር በደብረ ሊባኖስ ጉባኤ ያደርጉና በሰኔ ወር ወደ እየሃገረ ስብከታቸው ይሠማሩ ነበር ።

4. ደብረ አስቦ የሚገኘው በሸዋ ክፍለ ሀገር በሰላሌ አውራጃ ከደብረ ሊባኖስ ገዳም በ2 ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት የሚገኝ ቦታ ነው ። ዛሬም ስሙ አልተለወጠም ።

* * *

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ

መንፈሳዊ ሰላምታዬን እያቀረብኩ የሚከተለውን ጥያቄ አቀርባለሁ ። ከሕዳር 15 እስከ ታኅሣሥ 28 ቀን እናቶችና አባቶች እንደዚሁም የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሲጾሙ እያለሁ በዚህ አጋጣሚም የእኔ እናትና የባለቤቴ እናት ልክ እንደ ዐቢይ ጾም ይጾማሉ ። ግን ሁለቱም ምክንያቱን አያውቁትም ።

ስለዚህ የዚህን ጾም ምክንያትና የሰኔን ወር ጾም ምክንያት ያብራሩልኝ ። እንዲሁም በልደትና በጥምቀት ዋዜማ ስለሚጾሙት ጾሞች ለምሳሌ የልደት በዓል ሰኞ ሲውል እሑድ የገሀድ ጾም ይጾማልን? ግን እንዴት ጓደኛዬ ገሀድ የሚሆነው ልደት ዐርብ ወይም ረቡዕ ሲውል ነው ብላ ተከራከረችኝ ለሁሉም እናንተን ጠይቆ መረዳት በጣም ጥሩ ስለመሰለኝ እንድታብራሩልኝ እጠይቃለሁ ።

አማረች ወርቄ

አዲስ አበባ

• ወ/ሮ አማረች ወርቄ ስለ ጥያቄዎ እጅግ እናመሰግናለን ከኅዳር 15-ታኅሣሥ 28 ቀን የሚጾመው ጾም እግዚአብሔር ወልድ እኛን ለማዳን ወደዚህ ዓለም መምጣቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ስለተወለደልደቱን ከማክበራችን በፊት ለመዘጋጀት ነው።በመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓትማንኛውም ታላቅ በዓል ለምሳሌ እንደ ልደት ጥምቀትና ትንሣኤ ሲከበሩ በቅድሚያ የዝግጅት ጾም ይደረጋል ። ይህንም ጾም በፊት ነቢያት በኋላም ሐዋርያት ጾመውታል ።

ከሐዋርያትም በኋላ እነሆ እስካሁን ድረስ እኛ እንጾማለን ። የሰኔ ወር ጾም ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ስለመንፈስ ቅዱስ ክብር የጾሙት ጾም ነው ።

የልደትና የጥምቀት ዋዜማ ጾም ደግሞ እርስዎ እንደ ጠቀሱት "ገሃድ" ይባላል ገሃድ ማለት የልደትና የጥምቀትን በዓል የሚገልጡ ድርጊቶች በዋዜማው ስለሚጾሙ ገሃድ ተብሏል ።

የሚጾምበት ምክንያት- 1ኛ ከላይ እንደገለጥነው መንፈሳዊ በዓልን በመንፈሳዊ ዝግጅት ለመቀበል ነው 2ኛ. የልደትና የጥምቀት ዕለት ሥርዐተ ቁርባን ሌሊት በዘጠኝ ሰዓት ስለሆነ ክርስቲያኖችም ቅዱስ ቁርባን መቀበል ስለሚገባቸው ከዚያ በፊት ማክፈል ይገባቸዋል ፣ 3ኛ. ልደትና ጥምቀት ረቡዕና ዐርብ በዋሉ ጊዜ እንደሌላው ቀን በሌሊት ስለሚቀደስ በለውጡ በዋዜማው መጾም እንደሚገባ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ተወስኗል ። ወይዘሮ አማረ

ወደ ገጽ ፲፱ የዞረ



www.ethiopianorthodox.org

# ከዐሥር አንድ ለእግዚአብሔር

(ዐሥራት)

<u>ክፍል 1</u>

ሰው ለእግዚአብሔር ታዛዥነቱን የሚገልጥባቸው ብዙ መንገዶች አሉ ፡፡ከብዙዎቹ አንዱ ከሚያገኘው ሁሉ ከዐሥር አንድ ማውጣት ነው ፡፡ በብሉይ ኪዳን ሕዝበ እግዚአብሔር ተብለው ይጠሩ የነበሩ እስራኤላውያን ከዐሥር አንድ ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ ታዝዘው ነበር ፡፡ ከዐሥር አንድ ለእግዚአብሔር አስተዋጽኦ ማድረግ በእስራኤላውያን ሥርዐተ ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን ከእነርሱ በፊትም ሆነ በሁዋላ በማንኛውም ሥርዐተ ሃይማኖት ዘንድ እንደነበር ሃይማኖታዊ ታሪክ ያስረዳል ፡፡

ሰው ለእግዚአብሔር ዐሥራት በሚሰጥበት ጊዜ የራሱን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ይሰጣል ፡፡ ለሰው የራሱ የሆነ አንዳች ነገር የለምና፡፡

በመዝሙረ ዳዊት 24፡1 ላይ "እነሆ ምድር መላዋ ለእግዚአብሔር ናት ዓለምና በውስጥዋ ያሉ ሁሉ ለእግዚአብሔር ናቸው" ተብሎ ተጽፎአል ፡፡ በዚህ መሠረት ማንኛውንም የእህልና የማዕድን አይነት የምናመርትባት ዕፅዋትንና አትክልትን አልምተን የምንጠቀምባት በጠቅላላ ተፈጥሮታውያን ነገሮችን ሁሉ የምናገኝባት ምድር ከእግዚአብሔር በነፃ የተሰጠችን ናት እንጂ ራሳችን በራሳችን የፈጠርናት አይደለችም ፡፡ በውስጥዋ ያሉትንም ነገሮች እንደሚያስፈልጉን ዐውቀን እኛ እምንበአልቦ አላዘጋጀናቸውም ፡፡ ፀሐይና ሌሎች ብርሃናት ሁሉ ውሆችና በውስጣቸው ያሉ ሀብቶች ሁሉ አየርም የእግዚአብሔር ናቸው እኛም እንድንጠቀምባቸው እግዚአብሔር በነፃ ሰጠን ፡፡

በመዝሙረ ዳዊት 50፡10-12 ላይ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል "የበረሃ አራዊት ሁሉ የእኔ ናቸው በሺህ ተራራዎች ያሉ እንስሳትም የእኔ ናቸው የሰማይን አዕዋፍ ሁሉ አውቃለሁ የምድረ በዳ አራዊት በእኔ ዘንድ ናቸው ዓለም በመላው የእኔ ነውና"

ዳዊት ለቤተ እግዚአብሔር ማሠሪያ የሚሆን ገንዘብና ጥሬ ዕቃ እርሱና ሕዝቡ ካዋጡ በኋላ በጸለየው ጸሎት እንዲ ይላል "...አምላክ ሆይ.. በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነው ባለጠግነትና ክብር ከአንተ ዘንድ ነው ፡፡..ሁሉ ከአንተ ዘንድ ነው ፤ ከእጅህም የተቀበልነውን ሰጥተንሀል ...አቤቱ አምላካችን ሆይ ለቅዱስ ስምህ ቤት እንሠራ ዘንድ ይህ ያዘጋጀነው ባለጠግነት ሁሉ ከእጅህ የመጣ ነው ሁሉም የአንተ ነው ..." (1 ዜና 29 ፡11-17)

እስከ አሁን የተመለከትናቸው ጥቅሶች ሁሉ ሰው ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው ስጦታ ከራሱ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር የእግዚአብሔር መሆኑን ያመለክታሉ ፡፡

እግዚአብሔር ማቴሪያልን (ቁሣቁስን) ብቻ አይሰጥም እግዚአብሔር ለሁሉ ሕይወትን ይሰጣል እንደ ተጻፈ በእግዚአብሔር ሕያዋን እንሆናለን በእግዚአቤሔር እንቀሳቀሳለን በእግዚአብሔር እንኖራለን (የሐዋ.17፡28) በዚህም የሕይወት ሁሉ ምንጭና መሠረት እግዚአብሔር እንደሆነ እንረዳለን ፡፡

"እግዚአብሔር ከሰማይ ዝናምን ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ሲሰጠን ልባችንንም በመብልና በደስታ ሲሞላው ራሱን ያለ ምስክር አልተወም" ይላል ሐዋርያው ጳውሎስ (የሐዋ.14፡17)

ለእግዚአብሔር ስጦታ ወይም ከዐሥር አንድ አስተዋጽኦ ከምናደርግባቸው መሠረታውያን ምክንያቶች አንዳንዶቹ በአጭሩ ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው ናቸው ፡፡ በተጨማሪም እግዚአብሔር ፈጣሪ ብቻ ሳይሆን የፈጠረውን ሁሉ ይጠብቃል እግዚአብሔር የሕይወት መሠረት ብቻ ሳይሆን ሕይወትን ከሚደርስበት መከራ ሁሉ ያድናል ፡፡

ስለዚህ የእኛ የሆነው ለእርሱ ስለሆነ የእርሱን ለእርሱ እንሰጣለን ፡፡ እኛንና የእኛ የሆነውን ሁሉ ፈጥሮ ስለሚጠብቅ የእርሱን ፈጣሪነት የእኛን ፍጡርነት ዐውቀን ለእርሱ ታዛዥነታችንን ለመግለጥ ከምናገኘው ሁሉ በፈቃዳችን ስጦታ እናደርጋለን ፡፡

<u>ክፍል 2</u>

<u>ለእግዚአብሔር ስጦታን በማቅረብ ለእኛ ጥሩ ምሳሌ የሆኑ ሰዎች</u>

በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት ውስጥ ለእግዚአብሔር ስጦታን በማቅረብ ከሚያገኙት ሁሉ ከዐሥር አንድ በመስጠት ምሳሌዎች የሆኑ ግለሰቦችና ማኅበሮች ብዙዎች ናቸው ፡፡ ከእነዚህም መካከል ለምሳሌ ያህል አንዳንዶችን እንጠቅሳለን ፡፡

<u>1. ቃየልና አቤል</u>

እነዚህ ሁለት ወንድማማች ከእህልና ከእንስሳ አስተዋጽኦ አድርገው ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዳቀረቡ በዘፍጥረት 4፡2-4 ላይ እናገኛለን ፡፡አቤል በጥሩ ፈቃድ ሲያቀርብ ቃየል በግዴለሽነት በማቅረቡ ስጦታው በማስመስገን ፈንታ አስወቅሶታል ፡፡

<u>2. አብርሃም (ዘፍጥረት 14፡20 ዕብ 7፡4</u>

አብርሃም ከረዥም ጉዞው መልስ በኋላ ለልዑል እግዚአብሔር ካህን ለነበረው መልከ ጼዴቅ ዐሥራትን ሰጠ ፡፡ አብርሃም በእግዚአብሔር ድልን ስለተጐናጸፈ ኃይልን ከእግዚአብሔር ስለአገኘ በምርኮ ካገኛቸው ነገሮች ሁሉ ዐሥራት አወጣ ፡፡ በነፃ ባገኘው ሀብት እግዚአብሔርን አከበረ ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ዐሥራት የመጀመሪያው ጥቅስ ይህ መሆኑ ነው ከሙሴ ሕግ በፊት በማንኛውም ሃይማኖታዊ ሕዝብ ዘንድ ዐሥራት ማውጣት የተለመደ እንደነበር በዚህ እንረዳለን ፡፡

<u>3. ያዕቆብ (ዘፍጥረት 28 .22)</u>

ያዕቆብ ወደአባቱ ቤት እግዚአብሔር በጤና ቢመልሰው ቢጠብቀው የሚበላውንና የሚለብሰውንም ቢሰጠው እግዚአብሔር ከሰጠው ሁሉ ዐሥራት እንደሚሰጥ ተሣለ ፡፡ እዚህ ላይ እናስተውል የያዕቆብ የዐሥራት አስተዋጽኦ ስለ ሦስት ዋና ዋና ምክንያታውያን ነገሮች ነው ፡፡ 1. ስለ ጤና "እግዚአብሔር በጤና ቢመልሰኝ" ይላልና 2. ስለ ጥበቃ" እግዚአብሔር ቢጠብቀኝ ይላልና 3. ስለ ፍላጎቱ መሟላት" እግዚአብሔር የምበላውንና የምለብሰውን ቢሰጠኝ ይላልና ፡፡ ታዲያ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለእኛ አሳጥቶን ያውቃልን?

የያዕቆብን የዐሥራት ስጦት ስንመለከት ከሙሴ ሕግ በፊት በነበሩ አባቶች (ፓትርያርኮች) ዘመን ዐሥራት መስጠት የተለመደ እንደነበር እናስተውላለን ፡፡

4. <u>እስራኤላውያን በሙሴ ዘመን (ዘጸአት 36፡2-7</u>)

ሙሴ ለመገናኛው ድንኳን አገልግሎት የሚውል ገንዘብና ጥሬ ዕቃ ሕዝቡ እንዲያመጡ አዘዘ ሕዝቡም በደስታ በፈቃዳቸው ከሚፈለገው በላይ ስጦታ ከማቅረባቸው የተነሣ "ከእንግዲህ ወዲያ የሚያመጣ አይኑር" የሚል ትእዛዝ በሙሴ ለሕዝቡ ተነገረ፡፡ይህን ታሪክ ስንመለከት እንደነቅ ይሆናል ፡፡ እርግጥ ዛሬም እውነተኞች ክርስቲያኖች ባሉበት ሀገር የእስራኤልአውያን የገንዘብ ስጦታ ታሪክ በድጋሚ ይታያል ፡፡

5. <u>እስራኤላውያን በዳዊት ዘመን (1 ዜና 29፡1-17</u>)

በዚህ ክፍል እስራኤላውያን ለቤተ መቅደስ ሥራ በፈቃዳቸው ብዙ የገንዘብና የቁሳቁስ ስጦታ እንዳደረጉ እናነባለን፡፡ ዳዊት ሕዝቡ ሁሉ በቅን ልብ ስጦታ ሲያደርጉ አይቶ እጅግ ተደሰተ ፡፡ አዎ የፈቃድ ስጦታ ሰጭውንም ተቀባዩንም እጅግ ያስደስታል ፡፡ የግዴታ ስጦታ ግን ማንኛውንም ክፍል አያስደስትም ፡፡

<u>6. ዘኬዎስ (ሉቃስ. 19፡1-8)</u>

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም በነበረበት ዘመን ሙዳየ ምጽዋት ዐሥራትና በቤተ መቅደስ መዝገብ ውስጥ ገንዘብ መጣል የተለመደ ነበር (ማቴ. 23፡23) ዘኬዎስ በጌታ ፊት ከገንዘቡ ሁሉ ግማሹን እንደሚሰጥ ተናዘዘ ጌታችንም ደኅንነት ለዘኬዎስ ቤት እንደሆነ እርግጠኛ ተስፋ ነገረው አዎ ከሚያገኙት ሁሉ ለእግዚአብሔር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ እውነተኛ ተስፋ አላቸው ፡፡

7. <u>ድሐዋ መበለት (ማር. 12፡41-44 )</u>

በእግዚአብሔር ዘንድ ድሓም ሀብታምም እኩል ነው እንደዚሁም ብዙም ጥቂትም ስጦታ በእግዚአብሔር ዘንድ እኩል ነው ፡፡ እግዚአብሔር የስጦታን ብዛትና አይነት ሳይሆን የልብን ፈቃድ ይመለከታል ፡፡ ስለዚህም ጌታችን ከሌሎች ስጦታ ይልቅ የመበለትዋን ስጦታ በአድናቆት ጠቀሰ ምክንያቱም ከልብ በመነጨ ፈቃድ ያላትን የሳንቲም መጨረሻ ያለ ስስት ሰጥታለችና ፡፡ ስድታዋም ለእግዚአብሔር ክብር እንደሚሆን እምናለችና ፡፡

8. <u>የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን (የሐዋ.2፡44-45)</u>

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ገንዘባቸውን ሁሉ በአንድነት ያደርጉ ነበር ፡፡ለእያንዳንዱም እንደ ፍላጎቱ ያካፍሉ ነበር (የሐዋ. 4፡32-35) ከእነዚህም መካከል ስሙ ተለይቶ የተጠራ በርናባስ ነው ፡፡ (የሐዋ. 4፡37) በርናባስ ከንብረታቸው ለእግዚአብሔር መንግሥት ለክርስቶስ የወንጌል ትምህርት ለሚያውሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ጠባቂ ቅዱስ እየተባለ እስከሁን በክርስቲያኑ ዓለም ይጠራል ፡፡

9. <u>በአሕዛብ መካከል የነበረች ቤተ ክርስቲያን (የሐዋ.11፡27-30)</u>

በሀገር ሁሉ ራብ በሆነ ጊዜ በይሁዳ የነበሩ ክርስቲያኖች በነገሩ አሰቡና ክርስቲያኖች ሁሉ ባስቸኳይ እንደየችሎታቸው አስተዋጽኦ አደረጉ ፡፡ በረኃብ ጊዜ የርዳታ አስተዋጽኦ ሲደረግ ይህ የመጀመሪያ ሪኮርድ ነው ፡፡ ይህ ከሆነ ከ12 ዓመት በኋላ ይህን የመሰለ አስተዋጽኦ የመቄዶንያ የአካይያና የገላትያ አብያተ ክርስቲያናት በኢየሩሳሌም ለነበሩ ቅዱሳን (ችግረኞች አስተዋጽኦ አድርገዋል ፡፡ (1 ቆሮ. 16፡1-2 ፤ 2 ቆሮ 8 እና 9 ምዕ)

<u>ለእግዚአብሔር ለምን እንሰጣለን?</u>

ይህን ጥያቄ ለመመለስ መጽሐፍ ቅዱስ ይረዳናል በቅድሚያም ብሉይ ኪዳንን እንመልከት ፡፡ ሕዝበ እግዚአብሔር እስራኤል ስለ ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ለእግዚአብሔር ዐሥራትና የነፃ ስጦታ ይሰጡ እንደነበር ተጽፎአል ፡፡

1.<u>ለአምልኮተ እግዚአብሔር</u>

አምልኮተ እግዚአብሔር ቀደም ብሎ በድንኳን ኋላም በቤተ መቅደስ ይፈጸም ነበር ፡፡ እነዚህ ሁለቱ የእግዚአብሔር ማደሪያዎች (ድንኳንና መቅደስ) የተሠሩ በሕዝብ የነፃ ፈቃድ ስጦታና ዐሥራት ነበር ፡፡ ለእነዚያ ቤቶች በሕዝቡ የልግስና ስጦታ በየጊዜው አስፈላጊው እንክብካቤ ይደረግላቸው ነበር ፡፡ ለምሳሌ ፡- (ሀ) ዘይት ለመብራት (ዘጸአት 27 20) (ለ) ዕጣን ለማዕጠንት (ዘጸአት 30፡36) (ሐ) ኅብስተ ገጸ ለቅዱስ ጠረጴዛ (መ) እንስሳት በዕየለቱ ለሚቀርበው መሥዋዕት (ዘጸአት 29፡38-42) ፡፡እነዚህና የመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ ለሥርዐተ አምልኮ መፈጸሚያ ከሕዝቡ ይቀርቡ ነበር ፡፡

2. <u>ካህናትንና ሌዋውያንን ለመርዳት</u>

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ካህናት ከሕዝቡ በሚሰጠው ዐሥራት እየተረዱ ይኖሩ ነበር ፡፡ ካህናትና ሌዋውያን ከሕዝቡ ጋር እንደ ሕዝቡ የመሬት ርስት አልነበራቸውም በዚህ ፈንታ እግዚአብሔርን በማገልገል ራሳቸውን መሥዋዕት አድርገው እንዲኖሩና የሚያስፈልጋቸውንም ከሕዝቡ እንዲያገኙ በብሉይ ኪዳን ተጽፎአል ፡፡ እንደዚሁም ማንኛውም እስራኤላዊ ከሚያገኘው ሁሉ ለ

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

ወይዘሪት አበራሽ አበበ እባላለሁ ፤ ከአዲስ አበባ ፤
የግንቦት ወር ትንሣኤ መጽሔትን ቁጥር 32 እንደ አጋጣሚ አግኝቶ በማንበብ ተደስቻለሁ ።
በተለይ የሴቶች አምድ በመኖሩ በበለጠ ደስታዬን ከፍ አድርጐታል ።

በዚሁ አምድ እንዲመልስልኝ አንድ ጥያቄ አቀርባለሁ ። ጥያቄዬም የክርስቲያን ሴቶች አኗኗር ከወጣትነት ጀምሮ እንዴት መሆን አለበት ?

የእውነተኛ ክርስቲያን ሴቶች አኗኗር ከሌሎቹ ሴቶች አኗኗር የሚለይበት መንገድ አለ ።በመጀመሪያ ግን ክርስቲያን ማለት ምን ማለት መሆኑን መረዳት ጠቃሚ ይመስለናል ። ክርስቲያን ማለት ክርስቶስን ያመነ ወንጌልን የተቀበለ ማለት ነው ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ራሱ ክርስቶስ ተብሎ እኛን ክርስቲያን አሰኝቶናል ።እንግዲህ ትእዛዙን የሚፈጽም መጽሐፍ ቅዱስንና የሊቃውንትን ትምህርት አምኖው የተቀበሉ በጠቅላላው አርአያውን የሚከተሉ ሁሉ ክርስቲያን ይባላሉ ። ክርስቲያን ምንም እንኳን ሰው ነውና ሳያውቅ ቢሳሳት ከትእዛዙ ውጭም ቢሰራ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ እንደሚገኘው ሁሉ ስለ ኃጢአቱ ተጸጽቶ የሚናዘዝና የሚተው ሰው ነው ።

ክርስቲያን የሌላውን የማይመኝ በህብረት ሠርቶ በህብረት የሚኖር ሌላውን እንደራሱ የሚያይ ከፈጣሪው በቀር በሌላ የማይመካ ተከፍሎ የሚበላ ነው። በተጨማሪም ክርስቲያን ሌላውን ለማገልገል እራሱን አሳልፎ ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ሰው ነው ።

ከብዙ በጥቂቱ ክርስቲያን እንዲህ ያለ ነው ። እውነተኞች ክርስቲያን ሴቶችም ያው ከላይ የተገለጸውን የሚፈጽሙ ናቸው ።

በጠቅላላው ያገቡም ሆኑ ያላገቡ ክርስቲያን ሴቶች በሚያደርጉት በሚናገሩት በሁለመናቸው ለሌላው ጥሩ ምሳሌ ሆነው መገኘት አለባቸው ።

እዚህ ላይ ክርስቲያን ሴቶች ስንል ያገቡትንና ያላገቡትን ሁሉንም ያጠቃልላል ግን በመጀመሪያ ለመግለጽ የምንፈልገው ስለ አላገቡት ክርስቲያን ሴቶች ነው ።

ያላገቡ ክርስቲያን ሴቶች በመጀመሪያ ለአቅመ ሔዋን ማለትም እስኪያገቡ ድረስ ማለት ነው ። ከሚፈጽሙት የሐሳብም ሆነ የሥጋ ፈቃድ ሁሉ በንጽህና ራሳቸውን እንዲጠብቁ ያስፈልጋል ። እርግጥ ነው በንጽህና ራሳቸውን መጠበቅ ስትሉ ምን ማለት ነው ? ከወንዶች ጋር አይነጋገሩ ? የወንድ ጓደኛ አይያዙ ማለት ነው ? ትሉ ይሆናል ነገር ግን የኛ አባባል እንደርሱ አይደለም ከወንዶች ጋር በማህበር ሥራ በመ/ቤት ሥራ በመንፈሳዊና አለማዊ ስብሰባዎች ልንገናኝና አብረንም ልንሠራ ልንማር እንችላለን ። ይሁን እንጂ አንዲት ወጣት ሰው አየኝ አላየኝ ብላ ተደብቃ ያለ ምንም ጥናትና ያለምንም መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ውል ክብሯን ማስደፈር የለባትም ማለታችን ነው ።

2ኛ አንዲት ክርስቲያን ወጣት ለወደፊት ኑሮዋን ከአንድ ክርስቲያን ወጣት ጋር ለመመስረት ካሰበች እንደ እስስት ሳትለዋወጥ በእውነተኛ ክርስቲያናዊ ፍቅር ማፍቀር ሲኖርባት ስለ ወደፊቱ ኑሮአቸው ሐሳብ ለሐሳብ በሚለዋወጡበት ጊዜም ከላይ እንደገለጽነው ከሥጋዊ ፈቃድ የራቁ ሆነው ቢገኙ አይከፋም ምክንያቱም እንደዚህ ያለው ጥንቃቄ የወደፊት ችግራቸውን ሊያቃልላቸው እንደሚችል አይጠረጠርም። ከእንደዚህ ያለውም ስህተት ሊወገዱ የሚችሉት ብዙ ጊዜ በገለልተኛ ሥፍራ ከመገናኘት የተቆጠቡ እንደሆነ ነው ።

3ኛ/ በጋራ ጥቅምና ዓላማ መስማማት ሲሆን ይህም አንድን ነገር ለወንዱ ወይም ለሴቷ ሲያደርጉ ለሁለቱም ወገን ጠቃሚና ተስማሚ አድራጐት መሆን ይኖርበታል ። ካልሆነ ግን መቅረት አለበት እንጂ በዓላማ መለያየትና መቃቃር ሊፈጥር ይችላል ።

4ኛ/ ክርስቲያኗ ወጣት የምትከተለው ወጣት በሃይማኖት የሚመስላት መሆን አለበት ካልሆነ ግን አንድነታቸው ያጠራጥራል በዛም ላይ ለወደፊት ለሚወለዱት ልጆች ማደናገሪያ ይሆንባቸዋል ።

5ኛ/ ይህች ክርስቲያን ወጣት ባቀደችው ሃሳብ መጽናት ይኖርባታል ። ይህም አንድ ወንድ ላንዲት ሴት ተብሎ በተጻፈው መሠረት ክርስቲያን ሴቶች ካንዱ ባል በስተቀር ሌላ ባለመመኘት በመከራም ሆነ በደስታ አብሮ መኖር ይጠበቅባታል ። ገንዘብ ሲኖረው ልትወደው ገንዘብ ሲያጣ ልትጠላው የክርስቲያን ሃይማኖት አይፈቅድላትም ።

እንግዲህ ይህች ክርስቲያን ወጣት ከሞላ ጐደል እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ከፈጸመች በኋላ የምትፈጽመው የጋብቻ ሥነ ሥርዓት በድብቅ ሳይሆን በጌታችን መድኃኒታችን ደም በተዋጀች በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ታውቆና በእርሱ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙ መሆን እንደሚገባው ማወቅ አለባት ከሁሉ አስቀድማ ግን ሃይማኖትንና ሥነ ምግባርን መጽሐፍ ቅዱስንና በማህበራዊ ኑሮ ሁሉ መልካም ክርስቲያናዊት ለመሆን የሚያበቃትን ትምህርት ማወቅ ይኖርባታል ። ዘወትርም በጸሎት መትጋት ከግዴታዎችዋ አንዱ መሆኑን መገንዘብ አለባት ።

ይህ እንግዲህ ከሞላ ጐደል ወጣት ክርስቲያን ሴቶች በእንዴት ዓይነት አኗኗር ወደ ጋብቻ ዓለም እንደሚያመሩ ሲያመለክት በሚቀጥለው ጽሑፋችን ደግሞ በትዳር ላይ ያሉ ክርስቲያን ሴቶች አኗኗር እንዴት መሆን እንዳለበት እንቀጥላለን ።



## ከእሥር አንድ . . .

ከገጽ ፱ የዞረ

ሌዋውያን ይከፍል ነበር ። (ዘኁል 18 ፡ 21-24 ፤ ዘዳግም 18፡1-5)

3. <u>ነዳያንን ለመርዳት</u>

ሕዝበ እግዚአብሔር እስራኤል ከሚያቀርቡት ዐሥራትና የነፃ ፈቃድ ስጦታ ሁሉ እየተከፈለ ለነዳያን እንዲሰጥ በሙሴ ሕግ ታዝዞአል (ዘዳግ 16፡11 ፡24 19 ፤ ዘሌዋ 19፡9-10 ዘዳግ. 14፡28-29 15፡11)

<u>በሐዲስ ኪዳን</u>

በሐዲስ ኪዳንም ክርስቲያኖች ስለ ልዩ ልዩ ብዙ ምክንያቶች ለእግዚአብሔር የዐሥራትና የፈቃድ ስጦታ ያደርጋሉ።



ሁሉ ከአንተ ዘንድ ነው ከእጅህም የተቀበልነውን ሰጥተንሃል።

ከብዙዎችም መካከል አራት ዋና ዋና ምክንያቶችን ቀጥለን እንገልጣለን ።

1. <u>ለአምልኮተ እግዚአብሔር</u>

አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጽምባት ቤተ ክርስቲያንን ለማነፅ ለማደስና ለመጠገን ሥርዐተ አምልኮት የሚፈጸምባቸው ዕጣን ፤ ጥዋፍ ፤ ወይንና ሥንዴ ለመግዛት ሌሎችንም ንዋያተ ቅድሳት ለማዘጋጀት ከምእመናን የዐሥራትና የፈቃድ ልግስና ያስፈልጋል ።

2. <u>አገልጋዮችን ለመንከባከብ</u>

"በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚያገለግል ማን ነው? ወይን ተክሎ ፍሬውን የማይበላ ማን ነው? መንጋ ጠብቆ ወተት የማይጠጣ ማን ነው? የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር ፤ ይህ ሁሉ የተባለ ስለወንጌላውያን አይደለምን"?
(1 ቆሮ. 9፡1-14 ፤ ገላ 6፡6 ፤1 ጢሞ. 5፡ 17-18 ፤ 3 ዮሐ. 5-8 ፤ ሮሜ 15፡25-28)
ተብሎ እንደተጻፈ፡- ምእመናን የጸና እምነት ፤ የቀና ምግባር እንዲኖራቸው ልጆቻቸው ግብረ ገቦች እንዲሆኑ ፤ የወላጆቻቸውን ዐሠረ-እምነት እንዲከተሉ በማስተማር ለሚተጉ ፤ ሥርዐተ ጥምቀት ተክሊልና ፍትሐት በመፈጸም ለሚያገለግሉ ካህናት መርጃ የሚሆን አስተዋጽኦ ምእመናን ሊሰጡ ይገባል ይህም ለምግብና ልብስ ለቤት ለጡረታ ለጤና ለልጆቻቸውም መንከባከቢያ ይከፈላል ።

3. <u>ለትምህርተ ወንጌል</u>

ወንጌል ለሁሉ እንዲዳረስ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ሑሩ ወመሀሩ. ...ሂዱና አስተምሩ" የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል ። ይህም ትእዛዝ በቤተ ክርስቲያን የሐዋርያነት ተግባር ይፈጸማል ። ይህንም ተግባር ለመፈጸምና ለማስፈጸም ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አባል የውዴታ ግዴታ አለበት ። በዚህ ተግባር የፊልጵስዩስና የመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት እጅግ ተመስግነዋል (ፊልጵ 1፡5 ፤ 4፡15) የጥንት ክርስቲያኖች፡- ገንዘብ ሲያዋጡ ቅድሚያ ለወንጌል ትምህርት ያደርጉ ነበር ። ዛሬም እንደዚያ ቢሆን እጅግ መልካም ነው ።

4. <u>ነዳያንን ለመርዳት</u>

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ሁልጊዜ ሙዳየ ምጽዋት ሲሰበስቡ ለነዳያን አንድ ማጥን ያስቀምጡ ወይም ያዞሩ ነበር የሚጣለውም ገንዘብ ለድሆች ይሰጥ ነበር ።

ድሆች የሚባሉ ፡- አባትና እናት የሌላቸው ሕጻናት ፤ የብዙ ጊዜ ሕሙማን ፤ ጠዋሪ የሌላቸው ሽማግሌዎችና ባልቴቶች ባል የሞተባት ባልቴት ሚስት የመተዳደሪያ መበለን (ብቸኛ) ወዘተ...ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን አባሎች ለሆኑ ችግረኞች ቅድሚያ ይሰጣል ።ስለዚህ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ነበረች (የሐዋ 6፡1) ። ክርስቲያኖች ለነዳያን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው ኀላፊነትም እንደአለባቸው ተጽፎአል (ማቴ.25፡40 ፤ ያዕ. 2፡15 ፤ ገላ.6፡10 ዕብራ 13፡16)

ምእመናን በክርስቲያናዊ ሥርዓትና በፈቃድ የሚያዋጡት ገንዘብ ለዚህ ብቻ ሳይሆን፡- ብዙ ምእመናን የሌሉባቸው አብያተ ክርስቲያናትን ለመርዳት ፡ ጥንታውያን ጽሑፎችን ለመጠበቅ የጥንቱን (ትውፊታዊውን) የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንደነበረ ለማቆየት ፡ የካህናት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት (ኮሌጅ) ለማቋቋም ፤ በገጠር ለሚኖሩ ኢአማንያን ወንጌላውያንን ለመላክና ለመሳሰሉት ጉዳዮች ሊውል ይችላል ። ሐዋርያትን ስለአስመላክ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጊዜ ታምታለች ። ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ እንኳን በመላ ኢትዮጵያ ለአፍሪካውያን ሁሉ የክርስትና እምነትን ማዳረስ ስትችል ምእመናንን የሚያስተባብርና ከእነርሱም የሚገኘውን ገንዘብ በሥራ ላይ የሚያውል የራስዋ የሆነ መሪ በማጣትና በሊቃውንቶችዋ አለመስማማት ሳትንቀሳቀስ ኖራለች ፤ ቢያንስ እንኳ ለምሥራቅ አፍሪቃ ሐዋርያትን መላክ ፤ አብያተ ክርስቲያናትን መሥራት ትችል እንደነበር ብዙ የውጭ ሀገር ክርስቲያኖች ይልቁንም አፍሪካውያን ተችተዋል ፤ ይተቻሉም ሆኖም ያለፈው አልፎአል ፤ ለወደፊቱ ግን ሊታሰብበት ይገባል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል 4

### ክርስቲያን ምን ያህል መስጠት ይገባዋል?

በሐዲስ ኪዳን ሕግ የሚኖር ምእመን እንደ ብሉይ ኪዳን ሰዎች በዐሥራት ብቻ ሳይወሰን በፈቃዱ ከዐሥር አራት ወይም አምስት ሊሰጥ ይችላል ። ምእመን ወንጌል በዐሥራት አይወሰንም ፣ ከዐሥር በአምስትም አይገደድም ፣ መስጠት እንደሚገባውም ራሱን አይቆጥርም ።

የክርስቲያን ስጦታ፦ (ሀ) ቻሪስ ልግስና ወይም ቸርነት (1 ቆሮ 16:3) (ለ) ካይኖኒያ=ኅብረት (2 ቆሮ 8:4) (ሐ) ዲያኮኒያ = አገልግሎት (2 ቆሮ. 8:4-9 (መ) ኤውሎጊያ= ምስጋና በረከት (2 ቆሮ. 9:5) ይባላል ።

ሐዲስ ኪዳን የፍቅር ሕግ እንደመሆኑ መጠን ሰዎች በፍቅርና በፈቃድ እንዲሰጡ ያዝዛል ። ግን ስለ ዐሥራትና ቀዳምያት ስለ በኩራትም በቀጥታ አያዝዝም ። ሆኖም ግንም ምእመን እንደ ችሎታው ይሰጥ ዘንድ ተፈቅዶአል ። ስለነፃ ፈቃድ ስጦታ በሐዲስ ኪዳን የተጠቀሱ ሰዎች ዘኬዎስ ደሃዋ መበለትና በርናባስ ናቸው እነዚህ ሰዎች ከዐሥር አንድ ሳይሆን ያላቸውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ሰጥተዋልና ።



ባለጠግነት ሁሉ ከእጅህ የመጣ ነው ሁሉም የአንተ ነው።

## ክፍል 5

### ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ምንድን ነው?

1- ራሳችንን፦ ከሁሉ በፊት ከእኛ የሚፈለገው ስጦታ ራስን የተቀደሰና ሕያው መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ማቅረብ ነው (ሮሜ 12፥፩) ይህንም በምሥጢረ ጥምቀት እንረዳለን ። አንድ ሰው በቅድሚያ ራሱን ወደ ጥምቀት ያስገባል እንጂ ከመጠመቁ በፊት ገንዘቡን አያቀርብም ። እግዚአብሔር እንደ ፈቀደ በእኛ አድሮ እንዲሠራ ራሳችንን ለርሱ ማስረከብ ከሁሉ የበለጠ ስጦታ ነው ። ቤታችን ለእግዚአብሔር አገልግሎት እንዲውል ማድረግ እንደታላቅ ስጦታ ይቆጠራል ። ለምሳሌ በቤተታችን እንግዶችን ብንቀበል ፣ ድሆችን ብንረዳ ለእግዚአብሔር ታዛዥነታችንን እንገልጣለን ። የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ ፣ ለመማርና ለመጸለይ ቤታችንን ለእግዚአብሔር ሰዎች ክፍት ብናደርግ እንደታላቅ አስተዋጽኦ ይቆጠራል ፣ ለዚህም የማርቆስ እናት ማርያም ታላቅ ምሳሌ ናት (የሐዋ.12:12)

2. ኃይላችንን፦ ሥራ የምንሠራበት ኃይል ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደተሰጠን በማመን በምንሠራው ሥራ ሁሉ እግዚአብሔርን ማክበር ይፈለግብናል፡ ሁሉን ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት ተብሎ አልና ።

3. ጊዜያችንን፦ ስለ ሌሎች በመጸለይ ፣ በማስተማር ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ ሥርዐተ አምልኮን በመፈጸም ችግረኞችን በመርዳት በሽተኞችን በመጠየቅ ፣ ጊዜያቸውን በሙሉ ለወንጌል ሥራ ላደረጉ ሰዎች በተወሰነ ሰዐት ሥራ መሥራት ለቤተ ክርስቲያን ገቢ ሊያስገኝ የሚችሉ ልዩ ልዩ የእጅ ሥራዎችን በመሥራት ከሳምንቱ በአንድ ቀን የተወሰነ ሰዓት መሥዋዕት ማድረግ ከዚህም ሌላ በተለየ መንገድ ከጊዜያችን ዐሥራት መስጠት እንችላለን ግን ከጊዜያችን ዐሥራት ስናወጣ በመንግሥትም ሆነ በሕዝባዊ ድርጅት ተቀጥረን ሕብረተ ሰቡን ከምናገለግልበት ጊዜ በመስረቅ አይደለም ።

4. የገንዘብ ስጦታ

ምእመናን ከገንዘባቸው በተለያዩ ምክንያቶች ሊሰጡ ይችላሉ ፣ ለምሳሌ፦በየሳምንቱ እሑድ የተቻላቸውን ያህል በሙዳየ ምጽዋት ይጥላሉ በየወሩ ደመወዝ የሚያገኙ ምእመናን ከዐሥር አንድ ወይም የፈቀዱትን ያህል ያዋጣሉ ። በንግድና በሌላ ሥራ የተሠማሩ ምእመናን ደግሞ በዓመት ወይም ከዓመት ሁለት ጊዜ የፈቃድ ስጦታ ያደርጋሉ ።

5. የምስጋና ስጦታ

የምስጋና ስጦታ ማለት አንድ ምእመን ስለተደረገለት መልካም ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን በማመስገን የሚያቀርበው የደስታ ስጦታ ነው ። ይህም በተለያየ ወቅት ይፈጸማል ። ለምሳሌ፦ (ሀ)ባልና ሚስት ልጅ በወለዱ ጊዜ (ለ) ልጃቸውን ባስጠመቁ ጊዜ (ሐ) በዘመን መለወጫ እግዚአብሔር ለአዲስ ዓመት ስላደረሳቸው (መ) ረዥም መንገድ ሄደው በሰላም በተመለሱ ጊዜ (ሠ) በዕለተ ልደት (ረ) በዕለተ ጥምቀት (ሰ) በጾም ጊዜ የቁርባቸውን ሂሳብ (ቀ) በዕለተ ትንሣኤ እና በመሳሰለው ልዩ በዓል ተስለው ስለታቸው በተፈጸመላቸው ጊዜ ልዩ ስጦታ በፈቃዳቸው ሊሰጡ ይችላሉ ።

6. የእህል ስጦታ

ይህ አይነት ስጦታ፦ በመከር ጊዜ ምድር ካፈራችው በረከት ከማንኛውም የእህል አይነት በቤተ ክርስቲያን አባላት የሚቀርብ ነው ። የእህሉ ስጦታ በአባላቱ ሲቀርብ ምእመናን በከፍተኛ ዋጋ ይገዙታል ፣ ወይም ተሰብስቦ በገበያ ለማንኛውም ገዥ ይቀርባል ።

7. የባለሙያዎች ስጦታ

የተለያየ የእጅ ሙያ (ተግባረ እድ) ያላቸው ምእመናን በየችሎታቸው ቤተ ክርስቲያን ሲሠሩ ትልቅ ስጦታ ይሆናል መሐንዲሱ ለመሠረተ ቤተ ክርስቲያን ፕላኑን በነፃ ወይም በመጠነኛ ዋጋ ያወጣል ፣ ግንበኛው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑን፡ ቤተ ልሔሙን ደጀ ሰላሙን ወዘተርፈ በመጠነኛ ዋጋ ይሠራል ፣ ሐ

በገጽ ፲፱ ይመልከቱ



## የሃይማኖት ዐምድ

> «ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፣ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፥፫) ።

### ለጥምቀት የሚያስፈልጉ ሦስት ዋና ዋና መሠረታውያን ነገሮች

1ኛ/ እምነት፡-የሚጠመቁት ሰዎች በዕድሜ ከፍ ያሉ ከሆኑ የክርስትናን ትምህርት ጠንቅቀው መማርና የክርስቶስንም አዳኝነት አምነው የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ለመቀበል አዲስ ሕይወት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል ።

የእምነት መግለጫ መክፈቻ ወይም መታወቂያ ማህተም ወይም ምልክት የሆነው ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ጣሪያና ግድግዳ ሆኖ የሚታነፀውና የሚዋቀረው በዚሁ በእምነት መሠረትነት ላይ ነው። ሊቃውንት የእምነትን ተቀዳሚነትና የምግባርን ተከታይነት በምሳሌ ሲያስረዱ 1ኛ እምነትን በሰው አካል ምግባርን በጥላ ይመስሉታል። ይኸውም ሰውየው በአካል ወደሚሄድበት ሁሉ ጥላው አብሮት ተከትሎት እንደሚዞር እምነትም ካለ ዘንድ ምግባር ተነጥሎ ሊታይ አይችልም። ስለዚህም አበው ሲናገሩ «ሃይማኖት ይቅደመኝ ፣ ምግባር ይከተለኝ ይላሉ፣ ።

2ኛ ሌላው ምሳሌ እምነት ጋሪውን በሚጐትተው የፈረስ ጉልበት ሲመስል ምግባር በተጎታቹ ጋሪ ወይም በሠረገላው ይመስላል። ሠረገላው ወይም ጋሪው ፈረሱ ወደ ሚሄድበት ሁሉ አብሮት እንደሚጓዝ ምግባርም ከሃይማኖት ሳይለይ ተጣማሪ/ ተከታይ/ ሆኖ እንደሚገኝ ያመለክታል። ስለዚህም አንድ ክርስቲያን የክርስቶስን አዳኝነት አሞኖ ምን መሥራትም እንዳለበት የሚገልጥና መንፈሳዊ ትምህርት ከተሰጠው በኋላ በተማረው ቃል በቅዱሳት መጻሕፍት ሕግና ትእዛዝ በመመራት ከክርስቶስ ጋር ያለውን የአንድነት ቀል ኪዳን ለማጽናት ይጠመቃል ።

2ኛ/ ጥምቀት በሥላሴ ስም ስለመሆኑ፦

ይኸውም በቅዱስ ወንጌል «እንግዲህ ወደ ዓለም ሁሉ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም እያጠመቃችሁዋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው»ተብሎ የተጻፈውን ያመለክታል። የእግዚአብሄር አንድነትትና ሦስትነት የተገለጠው በጥምቀት ነው። ስለዚህ በባሕርይ በመለኮት አንድ አምላክ የሆነውን በአካል በግብር በስም ሦስት ብሎ ማመን የያንዳንዱ ክርስቲያን ዋና መታወቂያ ምልክቱ ነው።

3ኛ ጥምቀት በውሃ ስለመሆኑ፦

ለሰው ሕይወት አስፈላጊ ከሆኑት ከዚህ ዓለም ዋና ዋና ነገሮች አንዱ ውሃ ሲሆን በየትም ሥፍራ ቢሆን በቀላሉ መገኘት የሚችል የተፈጥሮ ሀብት ነው። ድኃም ሆነ ሀብታም በቀላሉ ሊያገኘው የሚችል ነው። ስለዚህም ያለምንም ዘር መድልዎ ለሁሉ መገኘት የሚችል በመሆኑ እንደ.ወል ንብረት ተቆጥሮ በውሃ መጠመቅ አስፈላጊ ሆነ። የመጻሕፍተ ሐዲሳት መተርጉማን እንደሚሉትም ጥምቀት በውሃ እንዲሆን የተወሠነበትን ምክንያት የሚገልጡ ምሳሌዎች አሉት ።

ይኸውም 1ኛ ውሃ ሰውነትን ከዕድፍ እንደሚያነፃ ጥምቀትም ከኃጢአት ዕድፍ የምንነፃበት መስተሥርይ ነው።

2ኛ/ ውሃ ለአዝርእትና አትክልት ሕይወትን ልምላሜንም ከአበባ እስከ ፍሬ የሚሰጥ እንደ መሆኑ ጥምቀትም አንድ ክርስቲያን በክርስቶስ ሲያምን በመንፈስ ቅዱስ ተሐድሶን እንደሚያገኝና የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆኑትን የበጎ ሥራዎች ፍሬ ለማፍራት የሚችልበትን ጸጋ እንደሚሰጠው ይገልጣል። ይህኑ መሠረት በማድረግ ጥምቀት ቀደም ብሎ በዘመነ አሪት ሲሠራበት የቆየ ሲሆን ለንስሐ ያህል ሲሰጥ የነበረው ጥምቀት ኃጢአትንወደ ማስተሰረይ ደረጃ ከፍ ብሎ ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ዋናውን ክፍል ይዞ የሚገኝ በመሆኑም ሠለስቱ ምዕት «ለ፡ኅጢአት ማስተሥረያ በተሠራች በአንዲት ጥምቀት እናምናለን» በማለት ጥምቀት ከአንድ ጊዜ በላይ የማይደገም መሆኑን አረጋግጠዋል ።

አንድ አማኝ በሚጠመቅበት ጊዜ ወደ ውሃው ጥልቀት መግባቱ ለቤዛ ዓለም ተሰቅሎ መራራውን የሞት ጽዋ የተቀበለለት ፈጣሪው ክርስቶስ ወደ መቃብር የመውረዱ ምሳሌ መሆኑን ያሳስበዋል ከውሃውም መውጣቱ የትንሣኤውን ምስጢር ያመለክታል።

ባጠቃላይም አሮጌው ሰውነት የሚታደሰውና የጠፋው ልጅነት የሚመለሰው የእያንዳንዱ አማኝ ሁለተኛ ልደት በሆነው በጥምቀት መሆኑን ሲያስገነዝብ ያመነ የተጠመቀ ይድናል። አምኖ ያልተጠመቀ ግን ይፈርድበታል ሲል ራሱ ክርስቶስ በወንጌል ተናግሮዋል/ማር.16፡16/።

ስለ ጥምቀት ምሥጢር ሰፋ ባለ ሁኔታ ለመረዳት በማቴ. ምዕራፍ 3 የኢትዮጵያ ሊቃውንት በአንድምታው ትርጉም ያቀረቡትን ትንታኔና እንዲሁም «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነትና ትምህርት ከተሠኘው መጽሐፍ በገጽ 103 -112 የቀረበውን ማስረጃ መመልከት ይጠቅማል።

ቄስ መክብብ አጥናው

### ደብዳቤዎች

ከገፅ ፮ የዞረ

ች ወርቁ እርስዎ የጠየቁዋቸው ጾሞች ሁሉ በቤ/ክርስቲያናችን ከታወቁት ከሰባቱ አጽዋማት የሚቈጠሩ ናቸው ። በሌላውም ዓለም ይጾማሉ በተለይም "ገሃድ" ቪጂል በመባል ይታወቃል ቪጂል ማለትም በላቲን ብርሃን ወይም በመቅረዝ ያለ መብራት ማለት ነው ። ይህም ብርሃነ ልደቱን ለማየት የሚደረገውን ዝግጅት ያመለክታል "እንኳን ለብርሃነ ልደቱ አደረሳችሁ ማለትም ከዚህ የተያያዘ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

# ይህን ያውቁ ኖርዋል ?

እጅጉ ረታ ።

በደቡብ ሲና ምድረ በዳ አካባቢ ባሕረ ሰላጤ ጫፍ ከዛሬይቱ የኤላት ወደብ አጠገብ የዛሬ 3000 ዓመትገደማ ፤ በዘመኑ የተደነቀ የሥራ እንቅስቃሴ የሚታይባት እንዲት የወደብ ከተማ ነበረች ። ታላቁ መጽሐፍ ኢጽዮን ጋብርያላታል። ነገ ቀዳ. ም. 9.26 ይመልከቱ።

ንጉሥ ሰለሞን ከምሥራቅ አፍሪካ የባሕር ጠረፍ አሕጉር ፤ ከአረብ ምድር፡ ከሕንድ ሐገር ሕዝቦች ጋር ለሚያደርገው የንግድ ግንኙነት የሚያገለግሉት መርከቦች ተሠርተው የሚወጡት ከዚች ቦታ ነበር ።

ከሌሎች ስፍራዎች ይልቅ ይች ቦታ፡ ለዚህ ተግባር ለምን እንደተመረጠች ያውቃሉ? ያለምክንያት አልነበረም። አካባቢው የብረታ ብረት ፤ የመዳብ ወዘተ ጥሬ ዕቃ እንደልብ የሚገኝበት መሆኑ ታውቆ ፤ ወዲሁም የቦታው አቀማመጥ በባሕር መገናኛ ረገድ ለንግድ ሥራ አመችነት ያለው መሆኑ ተደርሶበት ነው ።

ዶክተር አልሰን ግሉክ የተባሉ የአርኪዎሎጂ ምሑር፤በዚች ቦታ ከ1938-39 ዓ.ም እ.ኤ.አ. ባደረጉት የቁፋሮ አሠሳ ይህን በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረውን ታሪክ እውነተኛነት የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ለማግኘት ችለዋል ። ከመርከቡ መሥሪያ ቤት በስተቀር የምርት ማከናወኛ መሣሪያዎች ማለት የአጉዶ ማንጉጃ ፤ የብረታ ብረት ማንጠርያ ማቅለጫና ወዘተ ፍራስራሾች ለዘመናት ከተቀበሩበት ሊወጡ ችለዋል ።

ከዚች ቦታ እንደ ሸክላ ሳህን፣ሚስግር የአሳ መንጠቆ የመሳሰሉ የምርት ውጤቶች እየተዘጋጁ በመውጣት ወደ ውጭ እየተላኩ በለውጡ የዝሆን ጥርስና የወርቅ ምንዛሬ ለሰሎሞን ያስገኙለት ነበር ።

የአርኪዎሎጂ ጥናት ምሑር ከ19 08-10 እንደ ኤ. አ በሰማርያ ምድር ባደረጉት የቁፋሮ አሰሳ ፤ አንድ በዝሆን ጥርስ ተጊጦ ተሰብጦ የተሠራ የቤተ መንግስት ፍራሽ ለማግኘት ችለዋል ይህም የሰማርያ ንጉሥ አክአብ ያሠራው መሆኑ ተረጋግጧል ። ነገ. ቀዳ. 22 39 ይመልከቱ፡፡ ከዚሁ ቤተ መንግሥት ፍራሽ ውስጥ ልዩ ልዩ ሕብረ ቀለም ካላቸው ከከበሩ ድንጋዮች /አዕናቁ/ የተሠሩ ትንንሽ ሳጥን ቢጤ ዕቃዎች ተገኝተዋል ። ዕቃዎቹም የአክአብ ሚስት ኤልዛቤል የዐይን ኩል የፊት ማበሻ ቅባቶች ከሰሚቲክስ የጥፍር ቀለሞች ማስቀመጫ መሆናቸው ታውቋል ነገ. ካልዕ 9 -30 ይመልከቱ

የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ የውሃ ማጠራቀሚያ ኩሬ አዘጋጅቶና መሬቱን ውስጥ ለውስጥ አስቆፍሮ ከአፈል ተራራ ሥር ካለችው የግዮን ምንጭ ወደ ቁድሮን ሸለቆ የሚፈሰውን ውሃ መንገዱን ለውጦ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ እንዲፈስ በማድረግ ያለው የውሃ እጥረት ችግር እንዲቃለል አድርጓል ። ነገ.ካልዕ 20፡20 ይህ ከዛሬ 2600 ዓመት በፊት የተሠራው የውሃ ማስተላለፊያ ቦይ ሥራው እጅግ አድካሚ ነበር ። ምክንያቱም ቦዩ የሚቆፈረው የድንጋዩ ቋጥኝ እየተቦረቦረ ከመሆኑም በላይ ፤ ይህም እንደዛሬ ዘመን በሞተር ኃይል በሚንቀሳቀስ መሣሪያ ሳይሆን ፤ በሰው ጉልበት በመሮና በመዶሻ ፤ በአካፋ ብቻ ይሠራ ስለነበር ነው ። ርዝመቱ ከምንጩ እስከ ውሃው ማጠራቀሚያ ድረስ 1700 ጫማ ሲሆን ፤ ቁመቱ 6 ጫማ ፤ ስፋት $2\frac{1}{2}$ ጫማ ነው። ፎቶክራፉን ይመልከቱ።

የዚህ ቦይ ውሐ የት እንደሚገባ ያውቃሉን? ምጥማቃተ ሰሊሆም ከተባለው መጠመቂያ ውስጥ ነው ምጥማቃተ ስሊሆም ጌታ የዕውሩን ዐይን በምራቁ ከቀባው በኋላ ሄዶ እንዲታጠብበት ታዞ የዳነበት ቦታ ነው ። ዮሐ. 9፡7 ።

በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ የውሐ እጥረት ችግር ስላለ ፤ በየዘመናቱ የተሠሩ 6 ያህል የውሃ ማጠራቀሚያና ማስተላለፊያ ቦዮች አሉ ። ከእነዚህም የመሬት ውስጥ ለውስጥና ከመሬት በላይ ያሉ ይገኛሉ ። ከእነዚህም ውስጥ ቤተ ሳይዳ የተባለውና ምጥማቃተ ሰሊሆም የተባለው ለመጠጥ ውህ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገራችን ፀበሎች ሕሙማን እየተጠመቁባቸው ይፈወሱ እንደ ነበር በታላቁ መጽሐፍ ተጽፏል ። ዮሐ. 5፡2 ። 9፡7 ።



ሕዝቅያስ በመሬት ውስጥ ለውስጥ ከአለት አስፈልፍሎ ያሠራው የውሃ ማስተላለፊያ ቦይ



ክርስቶስ በዕለተ ሐሙስ ወይኑን ወደ ደሙ ገቦነት የለወጠበትን ዕውነተኛ ጽዋዕ በውስጡ የያዘ የብር ጽዋዕ

ይህ ፎቶግራፉን የምታዩት ጽዋ ከንጹሕ ብር /ማቴርያል/ የተሠራ ነው ።

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



# ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ

በጌታ ዙፋን ዙሪያ የሚቆሙ ሃያ አራት ሊቃናት (ሽማግሌዎች) እንዳሉ በዮሐንስ ራእይ ብቻ ተጽፎአል ። እርግጥ በጌታ ዙፋን ዙሪያ የሚቆሙና የሚያመሰግኑ 24 (ሊቃናት) ሽማግሌዎች ብቻ ሳይሆኑ የሰው ልጅ ሊቆጥራቸው የማይችላቸው ሠራዊተ መላእክት እንዳሉ ሌላው ባለራእይ ዳንኤል ይነግረናል።

በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሃያ አራት ሊቃናት ካህናተ ሰማይ በሚል ስም ይጠራሉ ። ይህም ስያሜ ሰማያዊ አምላክን የሚያገለግሉ መሆናቸውን ያመለክታል ። ነገር ግን ጌታን የሚያመሰግኑ መላእክት በቁጥር የማይወሰኑ ሲሆኑ እነዚህ በ24 ለምን ተወሰኑ? የሚል ጥያቄ ይነግ ይሆናል ።አዎ ፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን ደብተራ ኦሪትንና መቅደሰ ኦሪትን ያገለግሉ የነበሩ ካህናት በአንድ ጊዜ ማገልገል እስከማይችሉ ድረስ ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ነበር ለምሳሌ የካህናቱ ቁጥር ብቻ 288 ያህል ነበር።በአንደኛ ዜና መዋዕል 24፡1-18 ተጽፎ እንደምናነበው ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንቱ ካህናት በ24 ሰሞን ተመድበው ቤተ መቅደስን ያገለግሉ ነበር ለአንድ ሰሞን የተመደቡትም ካህናት 12 ነበሩ ። ለእያንዳንዱ የሰሞን ቡድን አንድ አለቃ ሲኖረው በጠቅላላ24 አለቆች ይሆናሉ ። እነዚያም ሃያ አራት ሊቃነ ካህናት ወይም 24 የአምላክ ቤት አስተዳዳሪዎች እየተባሉ ይጠሩ ነበር (1 ዜና 24፡5) ሌዋውያንም እንደ ካህናት በ24 ሰሞን ተመድበው ቤተ መቅደስን ያገለግሉ በጽናጽልና በከበሮ በበገናና በመስንቆ ያመስግኑ እንደነበር በ 1 ዜና 25፡9-31 ተጽፎአል ።

እንግዲህ ዮሐንስ በራእዩ ያያቸው ሃያ አራት ካህናተ ሰማይ እነዚያ በ24 ሰሞን ተከፍለው በሃያ አራት ሊቃነ ካህናት ይመሩ የነበሩ ካህናተ ኦሪት እንደሆኑ የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት ይተረጉማሉ ። ይህንም ለማረጋገጥ ዮሐንስ ካህናቱን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን የኪዳኑን ታቦት ጨምሮ በራእዩ አይቷል (ራእይ 11፡16-19) ከእነዚህም ሌላ ዮሐንስ ዐሥራ ሁለቱን የብሉይ ኪዳን ፓትርያርኮችና ዐሥራ ሁለት የሐዲስ ኪዳን ፓትርያርኮችን በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም በበሮቿና በመሠረቶችዋ ላይ አይቷል ። እነዚህም በድምር 24 ይሆናሉ እንግዲያውስ 24 ካህናተ ሰማይ የተባሉ እነዚህም ሊሆኑ እንደሚችሉ በተዉማሪ ሊቃውንት ያስረዳሉ (ራእይ 21 12-14)

የኢትዮጵያ የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንትም ዮሐንስ በራእይ ያያቸው ሰማያውያን መላእክት እንደሆኑ ሀሳባቸውን ይወስኑና 24 መባላቸው ደግሞ በሃያ አራቱ ሰዓታት ያለማቋረጥ ስለሚያመሰግኑ ነው በማለት ያትታሉ ።

እዚህ ላይ የካህናቱ ቁጥር 24 ስለመሆኑ ያለውን ሐተታ እናቆይና ስለአገልግሎታቸው ባጭሩ እንመልከት፡-

1- <u>ለእምላክ የሚያቀርቡት አገልግሎት</u>

በዙፋን ላይ ለተቀመጠው ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ሕያው ለሆነው አምላክ እየሰገዱ "አንተ ሁሉን ፈጥረሃል ሁሉም በአንተ ፈቃድ ሆናአል ስለዚህም ለአንተ ክብር ኃይልና ውዳሴ ይገባሃል" እያሉ ሁልጊዜ ያመሰግናሉ (ራእይ 4፡10-11)

2.- <u>ለሰው ልጆች የሚያደርጉት አገልግሎት</u>

በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎችን በተለያየ መንገድ ያገለግላሉ ፤ ለምሳሌ የቅዱሳንን ጸሎት ወደ እምላክ ያቀርባሉ ኃዘንተኞችን ያጽናናሉ (ራእይ 5፡5-6) የተሰወረውን ራእይ ለቅዱሳን ይተረጉማሉ ፤ (ራእ 7፡13-14)

3- <u>ክብራቸው</u>

ሃያ አራቱ ካህናት በጌታ ዘንድ ታላቅ ክብር አላቸው ይኸውም ነጭ ልብስ ለብሰው አክሊል ተቀዳጅተው በጌታ ዙፋን ዙሪያ 24 ዙፋኖች ተዘርግተውላቸው እንዲቀመጡ ክብር የተሰጣቸው መሆናቸውን ዮሐንስ በራእዩ ደጋግሞ ይናገራል ።

ስለ ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ያለንን ሀሳብ እንደሚከተለው እናጠቃልላለን ሃያ አራቱ ካህናት ሰማያዊ አምላክን የሚያመሰግኑ ሰማያውያን መላእክት ናቸው ። በምድር ያለ መንፈሳዊ አገልግሎትና አንዳንድ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በእነርሱ አገልግሎት አንጻር ተመሥርቶአል ። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኦርቶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅሌትን ብንመለከት በቆመ ብእሲ 6 በዓምደ ወርቅ 6 ፤ በቀኝ ከበሮ ቤት 6 ፤ በግራ ከበሮ ቤት 6 ፤ መዘምራን እንዲቆሙ መደንገጉ በ24 ካህናተ ሰማይ ምሳሌ የተደረገ ነው ።

አንዳንድ ጊዜም በ24 ቀዳስያን መቀደሱ ፤ ዕጣን የሚታጠንበት የጽናው ሻኩራዎችም 24 መሆናቸው በሰማይ ጌታን የሚያመሰግኑ 24 ካህናት መናራቸውን ለማመልከት ታስቦ ነው ።

ከዚህም ጋር ስለ ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ የሚሰጠውን አንዳንድ የተሳሳተ አስተያየት እንቃወማለን ፤ ለምሳሌ ባቢሎናውያን 24 የኮከብ አማልክት ነበሩአቸው ይህም በታሪክ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ እስራኤላውያን ይህን አሳብ ከጐረቤቶቻቸው ተማሩ ። በእነርሱም አንጻር 24 ሊቃነ ካህናትን መደቡ ፤ የሚለውን ሀሳብ ፈጽመን አንቀበልም ። በሁለተኛም መንገድ 24 ካህናት የተባሉ ራሳቸው አርባዕቱ እንስሳ ናቸው ። ምክንያቱም ለእያንዳንዳቸው 6 ክንፎች አሉዋቸውና ሁሉም ክንፎቻቸውን ሲዘረጉ 24 ይሆናሉ በሚለው ትችት አስተያየታችንን እንጨምርም ።

እኛ ግን ቅዱስ ዮሐንስ ያያቸው 24 ቅዱሳን መላእክት በተጻፈው መሠረት ለሰው ልጆችና ለእንስሳት ምህረትን ከአምላክ የሚለምኑ ፤ የምእመናንን ጸሎት ወደ አምላክ የሚያቀርቡ እውነተኞች አማላጆች ሰዎችን የሚያገለግሉ መላእክት እንደሆኑ እናምናለን እናስተምራለንም ።



www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያን በሕብረተሰብ

ቤተ ክርስቲያን በሕብረተሰብ ለሕብረተሰብ የተቋቋመች እንደመሆንዋ መጠን የምትሠራውም ለሕብረተሰብ ነው ። ለምሳሌ ቀይ መስቀል ጾታን ፣ ዘርን ፣ቀለምን ፣ ሃይማኖትን ሳይለይ ችግር ለደረሰበት ለሰው ዘር በሙሉ እንዲያገለግል ፣ ሕብረተሰቡንም ለመርዳት እንደ ተቋቋመ ግልጽ ነው።

በዚሁ አንፃር ዓለም አቀፍ የሆነችው ቤተ ክርስቲያንም ጾታን ፣ ዘርን ፣ ቀለምን ፣ ሃይማኖትን ሳትለይ ችግር ለደረሰበት ሕብረተሰብ ሁሉ በተቻላት መጠን ትረዳለች ። ይኅውም በየዘመኑ በሰው ልጆች ላይ ብዙ ታላላቅ ጦርነቶች ተፈጽመዋል በብዙ ሥፍራዎችም ታላላቅ ጥፋትና ጉዳት በየጊዜው ደርሷል በድርቅ ምክንያት በየጊዜው ብዙ ሰዎች ተርበዋል በየሃገሩም በምድር መናወጥ፣ በጎርፍ በአውሎ ነፋስ የተነሳ ብዙ ሀብት ጠፍቷል ብዙ ቤትም ፈርሷል

ይህ ሁሉ ችግር በሰው ዘር ላይ በደረሰ ቁጥር ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ ፣ የልብስ የቁሳቁስም አስተዋጽኦ እያደረገች ሕብረተሰቡን ትረዳለች ወላጅ የሌላቸውንም ሕፃናት እየተማሩ እንዲያድጉ በእንክብካቤ እንዲኖሩ ታደርጋለች በዚህ ብቻ ሳትወሰን የዘር መድሎን የቅኝ ግዛትን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን አንዱ በሌላው መበዝበዝን ታወግዛለች የጦር መሣሪያ ቅነሳ እንዲደረግ በየጊዜው ለሚመለከታቸው ክፍሎች ሁሉ አስተያየትዋን ታቀርባለች በዓለም ላይ ከጦርነት ይልቅ ሰላም እንዲሰፍን የጦርነት መሣሪያዎችም ወደ ልማት ተለውጠው የተራበው እንዲጠግብ ፣ ያጣው እንዲያገኝ ሁሉም በእኩልነት እየሠራ እንዲኖር በየጊዜው ትሰብካለች።

ቤተ ክርስቲያን ይህን ሥራ በምትሠራበት ጊዜ ሁሉ የተራቡና የተጠሙ የተቸገሩና የታረዙ ፣ ሕብረተሰቦች ቢኖሩ ወደ እኔ ይምጡ ብቻ አትልም እራስዋም ወደ እነርሱ እየሄደች የችግራቸው ተካፋይ ትሆናለች ወዳልተማሩት እየሄደች የዕውቀት ብርሃን እንዲያገኙ የዕውቀት ፀጋ እንዲደርሳቸው ታደርጋለች የታመሙ እንዲፈወሱ ከማንኛውም ኑሮ አዘቅት ውስጥ ተላቀው የአንዱ መኖር ለሌላው መከራ እንዳይሆን ሁሉም በእኩልነት ሰርተው ተረዳድተው እንዲኖሩ የአንዱን ችግር አንዱ እንዲሞላው ታሥተምራለች ።

የምትሠራውና የምታስተምረውም ቅዱስ ጳውሎስ የጻፈውን መሠረት በማድረግ ነው ቃሉም እንዲህ ይላል ‘ለሌሎች ዕረፍት ለእናንተም መከራ እንዲሆን አይደለም ትክክል እንዲሆን ነው እንጂ የእነርሱ ትርፍ ደግሞ የእናንተን ጉድለት እንዲሞላ በአሁኑ ጊዜ የእናንተ ትርፍ የእነርሱን ጉድለት ይሙላ በትክክል እንዲሆን እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ ብዙ ያከማቸ አላረፈም ጥቂትም ያከማቸ አላጐደለም” 2ተኛ ቆሮንቶስ ምዕ.8 ከቁጥር 13-15

ቤተ ክርስቲያንም ይህን የሐዋርያውን አባባል የተከተለችበት ዋና ዓላማ ከርስ በርስ መለያየት ይልቅ ተባብሮ በጋራ እየተረዳዱ መሥራት እንደሚያስፈልግ ሕብረተሰቡን ለማስገንዘብ ነው እንደተባለውም አንድ ሕብረተሰብ ከታላቅ የዕድገት ደረጃ ሊደርስ የሚችለው እያንዳንዱ ለሁሉ ሁሉ ለእያንዳንዱ በሚለው ዓላማ ተባብሮ የሠራ እንደሆነ ነው ። ይሁን እንጂ አሁን ባለንበት ዘመን በአንዳንዱ ክፍለ ዓለም ከመጠን በላይ የሆነ ሙላትና ትርፍ ሲታይ በሌላው ላይ ደግሞ ከመጠን በላይ የሆኑ ጉድለቶች ይታያሉ አንዱ ከመጠን በላይ ሃብታም ነው ሌላው ከመጠን በታች ድሃ ነው ለአንዱ እረፍትና ሕይወት አለው ሌላው ደግሞ በፍጹም ችግር ላይ ይገኛል ። ቤተ ክርስቲያን ግን ለሌሎች ዕረፍት ለእናንተ መከራ አይሁን ለሌሎች ዕረፍትና ደስታ አይብዛ በእናንተም መከራና ችግር አይብዛ ግን ሁሉም ሕብረተሰብ በእኩልነት ይኑር ትላለች ታላቁ መጽሐፍም የእነርሱ ትርፍ የእናንተን ጉድለት ይሙላ የእናንተም ትርፍ የእነርሱን ጉድለት ይሙላ ይላል ።

ይህ እንግዲህ እግዚአብሔር የሚፈቅደው ጉዳይ ነው በአንዱ ያለው ችግር እስከ ሞት ደረጃ መድረስ የለበትም በሌላ ዘንድ ያለው ጥጋብም እግዚአብሔርን እስከ መርሳት ደረጃ መድረስ የለበትም ሁሉም በመረዳዳት ችግርን እንዲያስወግዱ ቤተ ክርስቲያን በሕብረተሰቡ ዘንድ እየተገኘች የምታስተምረው ሁሉም እርስ በርስ እንዲረዳዳ በማለት ነው ። ይህ እንግዲህ በዓለም አቀፍ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ስለ ሕብረተሰቡ የምታደርገው ትራድኦ ሲሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሕብረተሰቡ የሚለውን ደግሞ እንመለከታለን ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለሕብረተሰብ በሕብረተሰብ የቆመች ፣ እንደመሆንዋ መጠን ባለፉት ጊዜያቶች እንዳሁኑ ጊዜ ስልጣኔ ባልነበረበት ዘመን በ15 ሽህ አብያተ ክርስቲያናት 15 ሽህ አስተማሪዎች (መሪ ጌቶች) ቁጥር የሕብረተሰቡን ልጆች በየመቃብር ቤቱና በየደጀ ሰላሙ ዘርና ሃይማኖት ሳትለይ ፊደል ፣ ጽሕፈት ፣እያስተማረች ግማሹን ለመምህርነት ፣ግማሹን ላስተዳደር ፣ ግማሹን ለፍርድ ዳኛ እያበቃች ሕብረተሰቡን ስትረዳ ኖራለች ። ልዩ ልዩ ሥዕል በመሳል ፣ ሐረግ በመጣል ፣ መጽሐፍ በመጠረዝ በመድጐስ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ መንፈሳዊ ቅርሶችን ለትውልድ አቆይታለች እንዳሁኑ ጊዜ ዘመናዊ የሕክምና መድኃኒት ባልነበረበት ወቅትም ለልዩ ልዩ ቁስል ማከሚያ የሆኑ የባህል መድኃኒት ዕፀዋትን እየሰጠች ሕብረተሰቡን ስትረዳ ቆይታለች ።

በአሁኑም ጊዜ ቢሆን የኢትዮጵያ ኦ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



# ጽዮን ታቦተ ሕግ ወኪዳን

ታቦት ማለት ማደሪያ ማለት ነው እግዚአብሔር የሕግና የኪዳ ን ቃሉን በመጀመሪያ ጊዜ ለሙሴ በደብረ ሲና የሰጠው በጽላቱ ላይ ጽፎ ነው ።

ልዑል እግዚአብሔር 10 ቃላትን በጽላቱ ላይ ጽፎ ለሙሴ ከሰጠው በኋላ ለጽላቱ መቀመጫ የሚሆን ታቦት እንደሚያስፈልገው ነግሮታል ፣ እንደ ነገረውም ወዲያውኑ ታቦቱን ለማዘጋጀት ችሏል ከዚያም በኋላ ሙሴ 10 ቃላት የተጻፈበትን ጽላት በታቦቱ ላይ በማስቀመጥ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበውን መንፈሳዊ አገልግሎት ሁሉ ይፈጽም ነበር ።

«በስመ ኀዳሪ ይጼዋዕ ማኅደር » በቤቱ ውስጥ በሚኖረው ስም ቤቱ ይጠራል እንደሚባለው ሁሉ ቆይቶ ጽላቱ በታቦቱ ታቦቱ በጽላቱ ስም ይጠራ ጀመር ይህ አጠራር በሀገራችን የተለመደ በመሆኑ አሁንም ቢሆን ጽላቱንና ታቦቱን ሁለቱንም በአንድ ላይ መጥራት አዲስ ነገር አይደለም ።

ሙሴ በደብረ ሲና ከእግዚአብሔር የተቀበላቸው 10ቱ ቃላትም የተጻፉ በጽላቱ ላይ መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል። እግዚአብሔር የቃሉ ማደሪያ በሆነው በታቦቱ ላይ እያደረ አማኞቹ እስራኤልን ይረዳቸው ነበር ። ሕዝ በእስራኤል ከጠላቶቻቸው ኢሎፍላውያን ጋር ለጦርነት በተሰለፉ ጊዜ እንዲሁም ሊያስወግዱት የማይችሉት ሌላ ችግር በገጠማቸው ወቅት እግዚአብሔር በታቦቱ ላይ አድሮ ስለሚረዳቸው መሣሪያ አድርገውና እጅግ በጣም ተመክተው የሚነሡት ታቦቱን ነው ።

በታቦቱ ላይ ያደረውም ኃይለ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ድል ያደርግላቸዋል ችግራቸውንም ያስወግድላቸዋል ይህ በሙሴ ዘመን ታቦት እየተባለ ይጠራ የነበረው የእግዚአብሔር ማደሪያ በዳዊት ጊዜ ታቦተ ጽዮን ተብሎ ተሰይሟል ።

ታቦተ ጽዮን የሚለውንም ሥያሜ ያገኘው ጽዮን ተብላ በምትጠራው እስራኤላውያን ከተማ ስም ነው ጽዮን ተብላ የምትጠራው የዳዊት ከተማም የተበደሉና የተገፉ ሕዝቦች ሁሉ እውነተኛ ፍርድ ለማግኘት ተሰብስበው በመጠጋት የሚሰነብቱባት ከተማ ስለነበረች በታቦትም ኃይል ብዙ ችግር የሚቃለል ስለሆነ ታቦቷ ታቦተ ጽዮን ለመባል በቅታለች ይባላል ።

ታቦተ ጽዮን ለእግዚአብሔር አማኞች ሁሉ ልዩ ልዩ ተአምራትን እንደ ፈጸመች ከቅዱስ መጽሐፍ እንረዳለን ታቦተ ጽዮን ከፈጸመቻቸውም ተአምራት አንዱ ኅዳር 21 ቀን በመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክ፡ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሚከበረው በዓል ነው የበዓሉን ታሪክ በአጭሩ እንመልከተው ።

ዘመኑ እስራኤላውያንና ኢሎፍላውያን ስምምነት ያጡበት ዘመን ነበር ሁለቱም ወገኖች ዘወትር ከመጋጨትና ከመጣላት አይቦዝኑም ነበር እግዚአብሔርም እሥራኤላውያን ሕጉን ሲጠብቁና ትዕዛዙን ሲያከብሩ በታቦተ ጽዮን እያደረ ሲረዳቸውና ጠላቶቻቸውን ድል ሲያደርጉ ሕጉን ሲያፈርሱና ሲያቃልሉ ደግሞ በረድኤት ይለያቸውና ለጠላቶቻቸው ተሸንፈው ይሸሻሉ ይማረኩሉም ።

በዚያ ዘመን ኤሊ የሚባል ሊቀ ካህናት ነበር ለእርሱም ሁለት ልጆች ነበሩት ስማቸውም አፍኒና ፊንሐስ ይባል ነበር አባታቸው ኤሊ በዕድሜ የገፋ የዘጠና ስምንት ዓመት ሽማግሌ ስለነበር የአባታቸውን ምክር አይቀበሉም ልጆቹ የአባታቸውን ምክርና ተግሣጽ እያቃለሉና እየሻሩ በራሳቸው አሳብ ብቻ ይመሩ ጀመር በሕዝብም ላይ የሚያደርሱትን በደል ከቀን ወደ ቀን እየጨመሩ ሄዱ ።

እግዚአብሔር ሕጉን ባፈረሱ ሰዎች ላይ የሚያዝዘው መዓት በሕግ አፍራሾች ላይ ብቻ ተወስኖ አይቀርምና በጠቅላላ ሕዝቡን ለመቅጣት አስፈለገ በእስራኤላውያን ላይ በአካባቢዎቻቸው ያሉትን ሰዎች ሁሉ በጠላትነት አስነሣባቸው በዚህ ጊዜ ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው የኤሊ ልጆች ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ ጦሩ ግንባር አመሩ በጦርነቱም ላይ አፍኒና ፊንሐስ ሲሞቱ ታቦተ ጽዮንም በኢሎፍላውያን እጅ ተማረከች ከእስራኤላውያን ሕዝብም እኩሉ በጦርነቱ ላይ ሲሞቱ እኩሉ ደግሞ ከጠላቶቻቸው ግንባር ሸሹ ከጦርነቱ ሸሽቶ ከሞት ያመለጠ አንድ ሰው እየሮጠ ወደ ኤሊ ሂዶ እስራኤላውያን ተሸንፈው መሸሻቸውን ሁለቱ ልጆቹ አፍኒና ፊንሐስ መሞታቸውንና ታቦተ ጽዮንም መማረኳን ነገረው ኤሊም ይህንን አስደንጋጭና አሳዛኝ ወሬ በሰማ ጊዜ እጅግ በጣም ሸምግሎ ነርርና ከተቀመጠበት ወንበር ወድቆ ተሰባብሮ ሞቷል ቀዳ. ሳሙኤል 4 ፡ 18 ።

ኢሎፍላውያን ታቦተ ጽዮንን ማርከው ከወሰዷት በኋላ ዳጐን ተብሎ ከሚጠራው ጣዖታቸው ጋር አስቀመጧት ያስቀመጧትም ታቦት ጽዮንን በሥር ዳጐንን በላይ አድርገው ነበር በበነጋው ለማየት ቢመጡ የዳጐን እግሩ ተቆርጦ ደረቱም ተሰባብሮ ታቦተ ጽዮን ግን ምንም ዓይነት ጉዳት ሳይደርስባት አገኙአት ኢሎፍላውያን በዚህ ሲናደዱ በሕዝቡ ላይ እበጥ እየወጣ ሲገድላቸው እኩሉ ደግሞ የሚያንቀጠቅጥና የሚጥል በሽታ እየያዛቸው በየመንገዱ እየወደቁ ይቀሩ ጀመር በተጨማሪም እህላቸውን አይጥ ሲየጠፋባቸው እንስሶቻቸውም በበሽታ አለቁባቸው ።

ታቦተ ጽዮን ይህንን የመሰለ ኃይለ ተአምር በኢሎፍላውያን ላይ እየፈጸመች በፍልስጥኤም ሀገር ለሰባት ወራት ኑራለች ከሰባት ወራት በኋላ ኢሎፍላውያን ታቦተ ጽዮንን ወደ ሀገሯ ሸኝተው ለመስደድ ተመካከሩና ለታቦተ ጽዮን

በገጽ 21 ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# ሊቃውንቶቻችን

## አለቃ ኪዳነ ወልድ ኤዎስጣቴዎስ

አለቃ ኪዳነ ወልድ የትውልድ አገራቸው በሸዋ ክፍለ ሀገር በተጉለት ወረዳ ውስጥ "ካሲማ" የሚባል ቀበሌ ሲሆን የተወለዱትም በአሥራ ሰባተኛው ምእት ዓመት መጨረሻ ላይ ነበር ።

በትምህርት አቋማቸውም በኩል በሙያቸው ከታወቁት ወላጅ አባታቸው ንባብና ዜማ ከተማሩ በኋላ ቅኔ ተቀኝተዋል ።

ወዲያውም የትምህርት ገጽታቸውን ወደትርጓሜ መጻሕፍት ጉባኤ መልሰው አፈር ባይኔ ከነበሩት ከመምህር ወልደ ሥላሴ ዘንድ የሐዲሳትንና የሊቃውንትን ትርጓሜ በሚገባ አጥንተዋል ።

የመጻሕፍተ ብሉያትንም ትርጓሜ ተምረዋል በአትሮንስ የተዘረጋ መጽሐፍ ከሁለት ሜትር ባላነሰ ርቀት ቆመው በማንበብ የታወቁት አለቃ ኪዳነ ወልድ በሰሙነ ሕማማት ግብረ ሕማማትን ሲያነቡ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ አይተው "ለመሆኑ እንዲህ አድርጐ የሚያነብ መልአክ ነው ሰው"? ብለው አድንቀዋቸዋል ።

ንጉሡ የትምህርትና የጠባይ ይዞታቸውን በዝርዝር ጠይቀው ከተገነዘቡ በኋላም በቤተ መንግሥት ሆነው ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ አድርገዋል ፤

### በሃይማኖት ምክንያት የደረሰባቸው ስደት

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በተዋህዶ እምነት የሁለት ልደትን ትምህርት የምትከተል ሁሉ የምገዛውን አገል ልቀት" ብለው ዓዋጅ በአናገሩ ጊዜ ከሸዋ ወደ ጐንደር ከዚያም ወደትግራይ ተሰደው አሥራ አራት ዓመታት ያህል ከገብየው ጳጳስ ከብፁዕ አቡነ ሰላማ ጋር ቆይተዋል ።

በስደት ላይ ሳሉም አባ ያዕቆብ የተባለ ካቶሊካዊ መነኩሴ ወደክፉ ክፍለ ሀገር ተሠማርቶ የሁለት ባሕርይን እምነት ለማስተማር በዙሪያው በትግራይ በኩል መሔዱን ቢሰሙ ሁኔታውን የዓፄ ዮሐንስ እናት ለነበሩት ለወይዘሮ ሥላስ አሳስበውና የሚረዱዋቸውን ሰዎች አሳዝዘው በማስገደድ ወደሀገሩ እንዲመለስ አድርገዋል ።

አለቃ ኪዳነ ወልድ ከአገራቸው ከሸዋ የተሰደዱት የሦስት ልደት ባህልን ነቅፈውና ጠልተው የሁለት ልደትን እምነት በመከተላቸው ብቻ ነበር ።

ይሁን እንጂ ተባርዮን የማያስቀር እግዚአብሔር "ሁለት ልደት ያላልክ ወይም በሁለት ልደት እምነት ያላመንክ" አይቀጡ ቅጣት እቀጣሃለሁ" የሚል ዓዋጅ በዓፄ ቴዎድሮስ እንዲነገር ስለአደረገ ዓዋጁ በዓዋጅ ተሻረ ፤ በዚህም ጊዜ ስደተኛው አለቃ ወደትውልድ አገራቸው ለመመለስ ዕድል አገኙ ።

ዓፄ ምኒልክ ለአሥር ዓመታት ዓፄ ቴዎድሮስ ዘንድ ቆይተው ወደሸዋ እንደ ገቡ "በሃይማኖት ምክንያት ከየአገራችሁ የወጣችሁና የተሰደዳችሁ ተመለሱ ፤ ሦስት ልደት ፤ ሁለት ልደት እያላችሁ መጣላታችሁን ተው ፤ ሁላችሁንም እንደየእምነታችሁና ባህላችሁ አስተዳድራችኋለሁ" ብለው ዓዋጅ በማናገራቸው አለቃ ኪዳነ ወልድ በተዋህዶ ሃይማኖታቸው ምክንያት በየአቅጣጫው ከሚደርስባቸው ልዩ ልዩ ተፅዕኖ ለመላቀቅ ችለዋል ።

ሆኖም አልፎ አልፎ አንዳንድ ተከታታይ ጠላት አላጡም ከብዙው አንዱም ቀጥሎ የተመለከተው ነው ዓኔ ምኒልክ ከመቅደላ ወደሸዋ በመምጣታቸው በቴዎድሮስና በምኒልክ መካከል ከፍተኛ ቂምና የጦር ዝግጅት መኖሩን የሚያውቁት የሦስት ልደት ባህል ተከታዮች በአለቃ ኪዳነ ወልድ ስም ወደ ዓፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤ ፃጽፉሉ ።

ጽሑፉም አድራሻ ከተሞላበት በኋላ "እኔ አገልጋይዎ ከዚሁ ሆኜ መምጣትዎን ተስፋ አድርጌ እለሁና ፈጥነው እንዲመጡ ይሁን"የሚል ሲሆን ይኸንኑ ሐሠተኛ ቃል የተሞላ ደብዳቤ መሰላቸውን መልእክተኛ በገንዘብ ተነጋግረው ወደዓፄ ቴዎድሮስ ይዞ እንዲሔድ ሲልኩት በመንገድህ "ገድም" ከሚባለው አካባቢ ስትደርስ አለቃ ኪዳነ ወልድ እንዲህ የሚል ደብዳቤ ለዓፄ ቴዎድሮስ አድርስ ብሎኛል እያልክ ለሕዝቡ ተናገር ይሉታል ።

መልእክተኛው እንደተነገረው ሁሉ ከተባለው ቦታ ደርሶ ወሬውን ስለአዛመተው የሰሙት ሰዎች ወዲያውኑ ይዘው ከነደብዳቤው ወደ ዓፄ ምኒልክ ያቀርቡታል ።

ዓፄ ምኒልክም ማነው ደብዳቤውን ሰጥቶ የላከህ? ብለው ላቀረቡለት ጥያቄ "የላኩኝ አለቃ ኪዳነ ወልድ ናቸው ፤ እኔም ካሽከሮቻቸው አንዱ ነኝ" የሚል መልስ ሲሰጥ ንጉሡ የአለቃ ኪዳነ ወልድን አሽከሮች ስም አንድ በአንድ በዝርዝር ንገረኝ ይሉታል መልእክተኛውም የአምስት ሰዎችን ስም ይነግራቸዋል ፤ የተጠቆሙት ሰዎች በአስቸኳይ እንዲቀርቡ ትእዛዝ ይሰጡና ሲመጡ ለየብቻቸው እንዲቀመጡ ያደርጋሉ ።

በማግሥቱ ንጉሡ በአደባባይ ለፍርድ ተገኝተውና ሐሠተኛውን መልእክተኛ አስቀርበው ሰዎችን ተራ በተራ እየጠሩ በመሠረቱ ሰውየውን የሚያውቁት መሆናቸውን ቢጠይቋቸው ከዚያን ዕለት በቀር ያላዩትና የማያውቁት መሆናቸውን ሲያረጋግጡ እሱ በበኩሉ ደግሞ የእያንዳንዱን ስም ቢጠየቅ እንዴሁ በወሬና በዝና እንጂ በቅርብ ያላጠናቸው በመሆኑ ያንዱን ስም ለሌላው በመስጠት ይናገራል ።



ከዚህ በኋላ ሐሰተኛ መሆኑ በጉልህ ስለታወቀ እውነቱን እንዲያወጣ ቢጠየቅ የሦስት ልደት ባህል ተከታዮች በገንዘብ ደልለውኝ ነው እንጂ ደብዳቤውን አለቃ ኪዳነ ወልድ አልሰጡኝም እነዚህንም ሰዎች በፍጹም አላውቃቸውም ብሎ የመጨረሻ ቃል በመስጠቱ በግርፋት እንዲቀጣ ተፈረደበት ።

አለቃ ኪዳነ ወልድ በትምህርታቸውና በሃይማኖት ጽናታቸው ባሳዩት ብርቱ ጥንካሬ የእነዋሪ ማርያምን አልቅና እንዲሁም የሸዋ ሊቀ ካህናትነት ሹመት ተሰጥቷቸዋል ፤ በሹመትም ሆነ ያለ ሹመት በኖሩበት ጊዜ ሁሉ የተማሩትን ከማስተማርና ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸውን ከማስተማር ያቋረጡበት ጊዜ የለም ።

### የሃይማኖት አፈጉባኤነታቸው

ዓፄ ዮሐንስና ዓፄ ምኒልክ (በዚያን ጊዜ ንጉሥ ምኒልክ) የሦስት ልደትና የሁለት ልደት እምነት ተከታዮችን ክርክርና ተቃውሞ በፍርድ ለመወሰን ግንቦት 21 ቀን 1870 ዓ.ም. በቦሩ ሜዳ በተገኙ ጊዜ ከእጨጌ ቴዎፍሎስ ጋር በረዳትነት መምህር አካለ ወልድ ሠርፀ ወልድ መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ አለቃ ተክለ ሥላሴ ሲጨመሩላቸው አለቃ ኪዳነወልድ ዋና አፈጉባኤ ሆነውና ተከራክረው የሦስት ልደት ተከታዮችን ረትተዋል

ይኸውም የሃይማኖት ጉባኤ ከተደረገ በኋላ በመንፈቁ ኅዳር 4 ቀን 1871 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ። አለቃ ኪዳነ ወልድ ለፈጸሙአቸው መልካም ሥራዎች ሁሉ መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ በአዲስ ዓለም በስማቸው አንድ ት ቤት ተሠርቶላቸዋል ።

አለቃ እምደ ጽዮን

## ቤተ ክርስቲያን . . .

ከገጽ ፲፯ የዞረ

ርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሕብረተሰብ ለሕብረተሰብ የተቋቋመች እንደመሆንዋ መጠን የተፈጥሮና የሰው ሠራሽ ችግር ለደረሰባቸው ሕብረተሰቦች እሩብ ሚሊዮን ብር ዕርዳታ ሰጥታለች ከዓለም አብያተ ክርስቲያናትም እርዳታ ጠይቃ ድርቅ ላጠቃቸው መርጃ የሚውሉ አምስት ላንድሮቨሮች ለርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን አስረክባለች በመሠረተ ትምህርትም ማይምነትን ለማጥፋት በተደረገው ዘመቻ የዘመቻው ተካፋይ ከመሆንዋም ሌላ በቅጥሯ ውስጥ የሚገኙትን ደጀ ሰላም ፤ የመቃብር ቤቶች ፤ የሰንበቴ ቤቶችን መማሪያ እንዲሆኑ ለሕብረተሰቡ አበርክታለች ።

ይህም አላማዋ በመሆኑ ወደፊት የተራበ ፤ የተጠማ ፤ የተቸገረ ሁሉ ወደ እኔ ይምጣ ማለት ብቻ ሳይሆን እሷ ራስዋ ወደ ተቸገሩት እየሄደች የተራበውን ማጥገብ የተጠማውን ማርካት ፤ የተቸገረውን ማስደሰት ያልተማረውን ማስተማር ይፈለግባታል ። እራሱ በራሱ ሠርቶ መኖርን እንዲያጠናና ሥቃይም ፡ችግርም በሥራ የሚወገዱ መሆናቸውን ጭምር ገልጾ ለሕብረተሰቡ ማስተማር ይገባታል በተጨማሪም እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ በሥራ በኑሮው እንዲሻሻልና በትሕትና የሚራመድበትን መንገድ ማሳየት አለባት ።

ይህም ሲባል ቤተ ክርስቲያን የጠፋውን በግ ወደ መንጋው መመለስ ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ለሰማያዊ ጽድቅ ዋስትናና የመስጠት ኀላፊነት እንዳለባት ሁሉ በምድር ላይ ያለውን ኩነኔ በማስወገድ ለሰው ልጅ ደህንነት ሌት ከቀን በመጣርና ሰዎች ሁሉ በእኩልነት ሠርተው የሚመገቡበትን መንገድ አሰልጥኖ ማሳየትም ከቤተ ክርስቲያን ይጠበቃል ።

አለቃ ነብየ ልዑል ዮሐንስ



## ከአሥር አንድ . . .

ከገጽ ፲፪ የዞረ

ናዊው የንጨት መስቀል የሻማ መቅረዝ ፤ መንበርና ጠረጴዛ በመሥራት ሙያውን ያበረክታል ። ብረቴው አትሮንስ ማጠፊያውንና መስገጫውን ሠርቶ በማቅረብ ፤ አንጥረኛው ፤ መስቀል ፤ዕርፈ መስቀል ፃህልና ጽዋ ወዘተ.. በመሥራት ሙያውን ለእግዚአብሔር ማበርከት ይችላል ።

ሸማኔው፡- ሰበኑን ፤ ማሕፈዱንና (ማሕደሩን) መጋረጃውን በማንም ሙያውን ያበረክታል ጥልፍ የመጥለፍ ችሎታ ያላቸው ሴቶች የመንበር ልብስ (የጠረጴዛ) መጋረጃ ሌሎችንም ጌጣጌጥ በመጥለፍ ቢያገለግሉ ታላቅ ስጦታ ይሆናል ። ሸክላ ሠሪዋ ሰን (ኩስኩስት)ምቅዳሐ-ማይ ፤ ዕእዱት ፤ ምክዳነ ዕዱት ብትሠራ ይህም እውነተኛ ዋጋማ ስጦታ ይ ይሆናል ። ጸሐፊና ሠዓሊ ደጓሺ ማህደር ሰፊና የመሳሰሉ ባለሙያዎች ሁሉ የተለያየ የሙያ አገልሎግት ሊያበረክቱ ይችላሉ ።

ቤተ ክርስቲያናችን አባሎችዋንና ሙያቸውን ለይታ ብታውቅ ከዚህ በላይ በጠቀስናቸው መንገዶች ሁሉ መጠቀም ትችላለች ። ምእመናንም በሙያቸውም በገንዘባቸውም ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ታማኞች ናቸው ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሁልጊዜ በዚህ አይነት ከመጠቀማቸው የተነሣ ከራሳቸው አልፈው ሌሎችን አብያተ ክርስቲያናት በገንዘብና ወንጌላውያንን በመላክ ይረዳሉ ። በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ የነፃ ትምህርት (ስኮላርሽፕ) በመስጠት የአዳጊ ሀገሮች አብያተ ክርስቲያናት ልጆችን በቴዎሎጂና በሌላም ትምህርት ያሠለጥናሉ ። እኛ ደግሞ በዚህ መጠን ሰንፈናል።ለምሳሌ፡-በራሳችን በመመካትና በመተማመን ፈንታ እንዲህ እንላለን "በዚህ ዓመት ከዚህ አገር ርዳታ አግኝተናል ለሚቀጥሉት ዓመታት ደግሞ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ይረዳናል ።" ግን ራሳችን በራሳች

ወደ ገጽ ፳፩ የዞረ



# የምእመናን ድምፅ

ይህ አምድ የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን በአስተዳደር ተሐድሶ የምትራመድበትና የምትሻሻልበት ክር ስቲያኖች ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው በቀና መንፈስ አስተያየት የሚያቀርቡበት ነው ። በዚህ ዓምድ ሊቀርቡ የሚገባቸው ጽሑፎች የቤተ ክርስቲያናችን ውሳኔዎች ሳይሆኑ የግለሰቦች አስተያየት መሆናቸውን የዓምዱ ተከታታዮች በቅድሚያ እንዲያውቁልን እንፈልጋለን ።

አዘጋጅ ነቅዓ ጥበብ ወንድም የስልክ ቁጥር 11-66-16 የመልእክት ሣ.ቁ. 3137 አዲስ አበባ

__በኤርትራ ሀገረ ስብከት__
__የሰበካ ጉባኤ አቋም__

የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ራሷን ያስችላል ተብሎ የታመነበት የሰበካ ጉባኤ በየአንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሲቋቋም ምእመናንም አስተዋጽኦ ሲያደርጉ መሆኑን በየጊዜው በቤተ ክርስቲያን ጋዜጦች ተደጋግሞ ተገልጿል ። ይህንንም በመገንዘብ በአንዳንድ አህጉረ ስብከት ከአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ በሀገረ ስብከት ደረጃ ሲቋቋም አንዳንዶች ደግሞ ኋላ ቀር በመሆናቸው የሚመለከተው ክፍል ሰሚናሮች በማካሔድ እንዲደረጁ በማድረግ ላይ ነው ።

በተለይ በዛሬው የምእመናን ድምፅ ዝግጅታችን በአሥመራ ከተማ በሀገረ ስብከቱ ጽ ቤት ተገኝተን ሊቀ ካህናት በላይ ገብረ ኤዎስጣቴዎስን የሰበካ ጉባኤ መምሪያ ኃላፊ ጠይቀን ያገኘነውን መልስ እናቀርባለን ።

__የምእመናን ድምፅ__ ሊቀ ካህናት በላይ በኤርትራ ሀገረ ስብከት የሰበካ ጉባኤ መቋቋም የጀመረው በስንት ዐመተ ምሕረት ነው?

__ሊቀ ካህናት__ ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ የተቋቋመባቸው አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት አሉ ከዚያ ወዲህ ም ያቋቋሙ አይታጡም በተለይ በጣም ሊቋቋም የቻቻለው በ1972 ዓ.ም ነው ።

__የምእመናን ድምፅ__ በኤርትራ ሀገረ ስብከት በስንት አብያተ ክርስቲያናት የሰበካ ጉባኤ ተቋቁሟል በተቋቋመባቸው አብያተ ክርስቲያናትስ በኩል የገንዘብ አስተዋጽኦው እንዴትነው?

__ሊቀ ካህናት__ በደንብ የተቋቋመባቸው 14 አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ። ሌሎችም በማቋቋም ላይ ይገኛሉ በአስተዋጽኦ በኩል ግን ሕዝብ ክርስቲያኑ ቀደም ብሎ አንዳንድ መንፈሳውያን ድርጅቶች በሚቋቋሙበት ጊዜ የገንዝብ አስተዋጽኦ ማድረግ ስለለመደ በዚህ በኩል ችግር አይኖርም የሚፈለገው አስተባባሪ ብቻ ነው ።

__የምእመናን ድምፅ__ የሰበካ ጉባኤ የተቋቋመባቸው አብያተ ክርስቲያናት በአስመራ ከተማ ባሉት ብቻ ነው ወይስ በሌሎች አውራጃዎች ጭምር ነው?



ሊቀ ካህናት በላይ ገ ኤዎስጣቴዎስ

__ሊቀ ካህናት__ ለጊዜው በሐማሴንና በሠራየ አውራጃዎች ነው በሌሎችም እነዚህን በመመልከት በማቋቋም ላይ ነው ያሉት በተለይ ይህ ሴሚናር ንቃት ስለሚሰጣቸው አሁን ተመልሰው እንዲሔዱ የሰሚናሩ ተካፋዮች እንደሚያቋቁሙ ተስፋ እናደርጋለን ።

__የምእመናን ድምፅ__ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የሰበካ ጉባኤ ከተቋቋመ በኋላ መሆን የማይገባቸው ምእመናን ፀሐፊ ሆነው እየሠሩ የቃለ አዋዲውን ደንብ እየጣሱ ችግር ፈጥረዋል። በእናንተ በኩልስ ጸሐፊው ካህን ነው ወይስ ከምእመናናን ነው?

__ሊቀ ካህናት__ በእኛ በኩል የቃለ አዋዲውን ደንብ በመከተል ለምእመናኑ የተወሰነ ምድብ ሥራ አላቸው ለካህናቱም እንደዚሁ ነው ጸሐፊ መሆን የሚችለው ካህን ስለሆነ እስከ አሁን ድ ድረስ ከምእመናን በኩል ጸሐፊ እንዲሆን የተመረጠ የለም

__የምእመናን ድምፅ__ የሰበካ ጉባኤ በየአንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሚቋቋምበት ጊዜ ችግር የፈጠረው የሰበካ ክልል በአንዳንዶች አብያተ ክርስቲያናት ባለመከለሉ ነው በእናንተ በኩል ይህ ዓይነቱ ችግር አለ ወይስ የለም?

__ሊቀ ካህናት__ የሰበካ ክልል ተከልሏል ግን አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም ምክንያቱም አንዳንዶችአብያተ ክርስቲያናት በዛ ያለ ክልል ሲያገኙ አንዳንዶች በጣም አነስተኛ ነው ያገኙት ያላገኙም አሉ ፣ እነዚህም በአካባቢያቸው ያሉትን ምእመናን ወደ እኛ መሆን አለባቸው እያሉ በመነጋገር ላይ ናቸው ።

__የምእመናን ድምፅ__ ፡ መቼም እኔ እንደሰማሁት የሰበካ ጉባኤ ክልል ያላቸው በአሥመራ ከተማ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ክልሉ የቀበሌ ማኅበራትን ክልል በመከተል ነው ወይስ ከዚህ ለዩት ያለ ነው?

__ሊቀ ካህናት__ የተጠቀምንበት የቀበሌ ማኅበራትን ክልል ነው ግን ከላይ እንደተጠቀሰው የመብዛት የማነስና ያለማግኘትም ስለአለ ጭቅጭቅ እስከትሎ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ ክስ የሔዱ አሉ ።

__የምእመናን ድምፅ__ የሰበካ ጉባኤ ክልል በምታደርጉበት ጊዜ የሀገረ ስብከቱ ጽ ቤትና የየአብያተ ክርስቲያናት ወኪሎች ብቻናቸው ወይስ የመንግሥት ተወካዮችም ተገኝተዋል?

ሊቀ ካህናት በመንግሥት በኩል የሚመለከታቸው ክፍሎች የማዘጋጃ ቤት የቀበሌ ማኅበራት ወኪሎች ተገኝተዋል ይረዳሉ የተባሉት አንዳንድ ግለሰቦችም በጥቆማ መልክ መጥተው አብረው ሠርተዋል

የምእመናን ድምፅ ሊቀ ካህናት በላይ እርስዎስ ክልሉ ጭቅጭቅ ያስነሣ ከሆነ ለወደ ፊት ይህን ለማሻሻል ምን ዕቅድ አላችሁ?

ሊቀ ካህናት ለጊዜው ይህ ክልል በካርታ ተነሥቷል ቢሆንም መንበረ ጵጵስናውም እምብዛም ስለአላመነበት እንደገና በጥናት ቢከለል ሊያወዛግብ አለመቻሉን እምናለሁ ይህም በቅርብ ጊዜ ውጤት እንደሚገኝ ገልጽ ነው ።

በኤርትራ ሀገረ ስብከት የሰበካ ጉባኤ አቋም ምን እንደሆነ ተረድተናል እንደተመለከትነው የሰበካ ጉባኤው መቋቋም እምብዛም ባይጠናከርም በሌላ በኩል ግን በአንዳንዶች ክፍላተ ሀገር ከተሞች ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ያልሠሩትን የሰበካ ጉባኤ ክልል ቅድሚያ ሰጥተውት ሲገኙ የሚያስመሰግን ነው ።

ምንም እንኳን ቤተ ክርስቲያን አንዲት መሆኗ ቢታወቅም የማዕከላዊ አሠራር ፈር እስከሚይዝ አንዳንዶች በከተማ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት በዚህ ዓይነት አመራር ቢሠሩ የሰበካ ክልል ሊያወዛግብ እንደማይችል እናምናለን ።

## ከአሥር አንድ ....

ከገጽ ፲፱ የዞረ

ን ላይ መመካት የምንችለው መቼ ይሆን?

__ማጠቃለያ__

ዛሬ እኛ በቀንም ሆነ በሳምንት በወር ወይም በዓመት ከምናገኘው ሁሉ ከዐሥር አንድ ወይም በከፊል ይልቁንም በሙሉ ለእግዚአብሔር ብንሰጥ እግዚአብሔር ላደረገልን ስጦታ ተመጣጣኝ ሊሆን አይችልም እግዚአብሔር አብ አንድ ልጁን እስኪሰጥ ሰውን ወደደ እግዚአብሔር ወልድ ሕይወቱን ለእኛ እስከ መስጠት ድረስ ወደደን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ በተነሣ በ50ኛው ቀን ተሰጠን ዛሬም ይሰጠናል ታዲያ የእኛ ስጦታ ከዚህ ሁሉ ጋር ይመጣጠናል? "ብቻ ስለማይነገር ስጦታ እግዚአብሔር ይመስገን" (2ቆሮ.9፥15

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

## ጽዮን ታቦተ ሕግ . . .

ከገጽ ፲፪ የዞረ

ካሣ የሚሆን ወርቅ በማጥን አድርገው ሁለት ላሞች እምቦሶች ያሏቸው እንቦሶቻቸውን ለይተው አስቀርተው በላሞቹ ላይ ሠረገላ ጭነው በሠረገላው ላይ ታቦተ ጽዮንንና ለእርሷ ካሣ የሚሆን ወርቅ በማጥን አድርገው ሸኝተው ወደ ሀገሯ ሰደዷት ፣

እስራኤላውያን የታቦተ ጽዮንን መመለስ በሰሙ ጊዜ በልልታ በሆታና በዝማሬ ተቀብለው አሚናዳብ ከሚባል ሰው ቤት አስገብተዋታል በዚያም ሰው ቤት 20 ዓመታት ኑራለች ቀ.ሳሙ.7፥2 በታቦተ ጽዮንም ምክንያት የዚያ ሰው ቤት እጅግ በጣም ተባርኮለት ደስ ብሎታል ዛሬ በሀገራችን በጥምቀት ዕለት ታቦቱ በእኛ አቅጣጫ ወርዶ ይደር ሲሉ ሌሎች ክፍሎች ደግሞ በእኛ አቅጣጫ መውረድ አለበት በማለት የሚከራከሩት ለአሚናዳብ ቤት የወረደውን በረከት መነሻ በማድረግ ነው ።

አሁን በታቦተ ጽዮን ስም የምትከበረው ቅድስት ድንግል ማርያም ናት ድንግል ማርያም ከእንስተ ዓለም ተመርጣ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ማደሪያ ስለሆነች በስሟ በተቀረጸው ታቦት ለእግዚአብሔር እንሰግዳለን እንማጸናለን ስዕለትም እንሳላለን በዘመነ ኦሪት በታቦተ ጽዮን ላይ በረድኤት እያደረ የአማኞችን ችግር የሚያቃልለው አምላክ አሁንም በታቦተ ማርያም በታቦተ ጻድቃንና በታቦተ ሰማዕታት በታቦተ መላእክት እንዲሁም በራሱ ስም በተሠየመው ታቦት የምንማፀነውን አማኞች ሁሉ ልመናችን እንደሚሰማንና ስዕለታችንና አገልግሎታችንም እንደሚቀበለን አንጠራጠርም ።

ስለዚህ በታቦተጽዮን እያደረ አማኞች እስራኤልን የረዳ እክዚአብሔር እኛን አማኞቹን ይረዳን ዘንድ ወደ እርሱ እንማፀናለን ።

ቄ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ



www.ethiopianorthodox.org

## ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን



በወጣትነህ ወራት ፈጣሪህን አስብ (መክ. 12-1)

### ወጣቶች በመንፈሳዊ ትምህ ርት

ብዙዎች ክርስቲያኖች ከሞት በኋላ ለሚጠብቁት መንፈሳዊ ሕይወት ብቻ ሳይሆን በሥጋዊ ሕይወት ዘመናቸውም ከኅብረተሰቡ ጋር በሥነ ሥርዓት በሰላምና በፍቅር የሚኖሩበትን ሕግ የማጥናት ግዴታ እንደ አለባቸው ያውቃሉ ይህንንም ግዴታ ለመወጣት ወጣቶች ልጆችቸውን ወደ ቤተክርስቲያን እየመጡ መንፈሳዊ ትምህርት እንዲማሩ ያደርጋሉ ወጣቶችም መንፈሳዊ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ወቅት ዐሠርቱን ቃላተ ኦሪትና ስድስቱን ቃላተ ወንጌል ከዚያም መሠረተ እምነት ካቲኪዝም እንዲያጠኑ ይደረጋል ።

አንዳንድ ጊዜም ወጣቶች መንፈሳውያን ጥናቶችን በመከታተል የሚገበዩት እውቀትና ሊያገኙ የሚችሉት ጥቅም ምንድነው? የሚያስከትልባቸው ጉዳትስ ብለው የሚጠይቁም ሊኖሩ ይችላሉ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ወጣቶች በቅድሚያ መንፈሳዊ ትምህርትን ከተማሩ ሕጋዊ ርምጃቸውን ይቀንሱና ከመሻሻል ወደ ኋላ ሊሉ ይችላሉ የሚል አንዳንድ ስንኩል ምክንያት ከፖለቲካ ጋር በማጣመር የሚያቀርቡም ይኖሩ ይሆናል ፤ ነገር ግን እነዚህን ጥያቄዎች የሚያቀርቡት ግለሰቦች ሁኔታውን በዝርዝር አጥንተው ወይም በቤተ ክርስቲያን የሚሰጡት ትምህርቶች ምን ዓይነት እንደሆኑና በማኅበራዊ ኑሮም በኩል ለኅብረተሰቡ የሚሰጡትን ጥቅምና ጉዳት ያልተረዱት ከመሆናቸው የተነሣ ፤ ነው እንጂ በቤተ ክርስቲያናችን የሚሰጠውን መንፈሳዊና የግብረ ገብ ትምህርት ያጠኑ ወጣቶች አብዛኛዎቹ ከልዩ ልዩ ወንጀሎችና ርካሽ ባህሎች ሁሉ ነፃ ከመሆናቸውም በላይ አገራቸውንና ወገናቸውን ከልብ የሚወዱ ናቸው የሞራል ውድቀትና ልዩ ልዩ ርካሽ ባህሎች ፤ በመንፈሳውያን ወጣቶች አይታዩም ፤ ሲሰኝነት ፣ ስካርና አመንዝራነት አያጠቃቸውም ፤ በአጠቃላይ ከመጥፎ ጓደኛ ጋር ውለው አጉል ልምዶችን አይለምዱም በመጥፎ ቦታም አይገኙም ይህንንም ጥንቃቄ የሚያደርጉት በተማሩት መንፈሳዊ ትምህርትና ዕውቀት የሚጠቅሙትንና የማይጠቅሙትን ነገሮች ከመረዳታቸው የተነሣ ነው ።

በመንፈሳዊ ሕይወታችን ኃጢአት ናቸው ብለን እንዳንፈጽማቸው የምንጠነቀቅላቸው መጥፎ ሥራዎች ሁሉ በምድራዊ መንግሥትና ሰብአዊ ሕግም የታወቁ ወንጀሎች ሆነው እናገኛቸዋለን ። ስለሆነም የሃይማኖት ሰዎች እነዚህ ርካሽ የሆኑ መጥፎ ልምዶችና የወንጀል አይነቶች በሃይማኖት መጽሐፍ የተወገዙ መሆናቸውን ስለሚያውቁና ከወጣትነት ዘመናቸው ጀምምረው በቂም ነገር ባጠኑት መንፈሳዊ ትምህርት ሊያደርጓቸው የሚገባቸውን ወይም እንዳይደርጓቸው የተከለከሉትን ነገሮች ጠንቅቀው ስለሚያውቋቸው በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ራሳቸውን በጥንቃቄና በጨዋነት እንዲመሩት ይገደዳሉ ። አንዳንድ ጊዜ ተሳስተው የሚፈጽሙት ወንጀል ቢኖር በስውር የሠራነውን ወንጀል ሁሉ መርምሮ የሚያውቅ እግዚአብሔር አይቶ እንደሥራችን ይፈርድብናል ብለው ስለሚያምኑ ስለ ጽድቅ ሲሉ ንስሐ ይገባሉ ሁለተኛም ይህንን የመሰለውን ኃጢአት ከመሥራት ይቆጠባሉ በዚህም ሳቢያ ከወንጀል ሁሉ ይቆጠባሉ ማለት ነው ።

ከዐሥርቱ ቃላተ ኦሪት ስለሰማያዊ ሕግ ማለት ስለአምልኮት ብቻ የሚነገሩት ከ4 አይበልጡም እነዚህም "ከኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ የአምላክህን ስም በከንቱ አታንሣ የሰንበት ቀን አክብር" የሚሉት ሲሆኑ ሌሎች ሕጎች ግን ሰማያውያንና ምድራውያን ናቸው ይህም ማለት በሰማይ ኃጢአት በምድርም ወንጀሎች ናቸው ማለት ነው ።

ለምሳሌ አትሥረቅ ፤ አታመንዝር አትግደል በሀሰት አትመስክር የባልንጀራህን ሀብትና ንብረት ያለሕግ ለመውሰድ አትመኝ የሚሉት ናቸው ፤ ታዲያ መስረቅ፡ በሀሰት መመስከር፡ ያለ ፍርድ መግደል ያልደከሙበትን ሀብት መቀማት በምድራዊ ሕግ ወንጀል እንደሆነ እንገነዘባለን በመንፈሳዊ ሕይወትም እነዚህ ነገሮች የታወቁ ኃጢአቶች መሆናቸው የታመነ ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ "ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ ፤ እናትና አባትህን አክብር" ስለሆኑ በምድራዊ መንግሥትም የሚደገፉ ናቸው ሥነ ሥርዓት የሚመነጨውም ከነዚሁ ነው እነዚህ ሕጋጋት ለሚፈጽማቸው የጽድቅ መንገዶች ከመሆናቸውም በላይ በምድራዊ ሥርዓትም የኅብረተሰቡን ሁኔታ የሚወስኑ ስለሆነም ወጣቶች እነዚህን ሕግጋት ከሕፃንነታቸው ጀምረው እንዲያጠኗቸው ቤተ ክርስቲያን ብርቱ ጥረት ታደርጋለች እነዚህን ለምሳሌ ያህል ጠቀስን እንጂ ወጣቶች በመንፈሳዊ ትምህርት የሚያጠኗቸው ብዙ ቁም ነገሮች እንዳሉ ልዩ ልዩ መንፈሳውያን መጻሕፍትን አገላብጠን ማየት ይቻላል ።

በሕብረተሰብ እድገትም የምንጠቀምባቸውና ስለማኅበራዊ ኑሮም የምንጠቅሳቸው ቁም ነገሮች አሉ እነዚህም የማይሠራ አይብላ 2ኛ ተሰ 3—10 ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑር ፤ ሮሜ12-18 ርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ ወንድሙን የሚጠላ ነፍሰ ገዳይ ነው ። 1ኛ/ዮሐ 3-11-15 ሌሎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን እናንተም ለሌሎች አድርጉላቸው ሌሎች ሊያደርጉባችሁ የማትወዱትን ደግሞ እናንተም በሌሎችም አታድርጉባቸው ማቴ 7-12" የሚሉትና የመሳሰሉት ናቸው ታዲያ እነዚህንና ሌሎቹንም የግብረገብ ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያን የተማሩ ወጣቶች ፤ እንኳን ራሳቸውንና ለጠቅላላው ኅብረተሰብ መልካም ምሳሌ ይሆናሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን ከዚህም ጋር ስለ ጽድቅ ብለው በሚፈጽሙት መልካም ሥነ ምግባር ምድራዊ ሕግጋትን ስለሚፈጽሙ የሕግ ተገዢዎች በመሆን አገራቸውን ና ወገናቸውን የሚያገለግሉ መልካም ዜጎች እንደሚሆኑ ይታመናል ። ስለዚህም ነው ቤተ ክርስቲያን«ልጆቻችሁን በመንፈሳዊ ትምህርት አሠልጥናችሁ በሥነ ሥርዓት አሳድጓቸው » እያለች ወላጆችን ዘወትር የምትመክረው ስለዚህም ይህንን ግዴታቸውን ለመወጣት ልጆቻቸውን ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት እየወሰዱ በሰንበት ቀንና በትርፍ ጊዜያቸው እንዲማሩ የሚያደርጉ ምን ያህል እንደሆኑ በትክክል ባናውቅም ቁጥራቸው በርከት ያለ ነው ።

የግብረገብ እውቀትን ካልገበዩት ከ ወጣቶች መካከል አብዛኛዎቹ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙና መጥፎ ጠባይ የሚታይባቸው ከመሆናቸውም በላይ አንዳንድ ጊዜም ከቤተሰብ ቁጥጥር ውጭ ሆነው ለሀገር ሸክም እስከመሆን ይደርሳሉና ወላጆች ቤተክርስቲያንና የሚመለከተው ሁሉ ሊያስቡበት ይገባል እንላለን።

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ



### ይህን ያውቁ ኖሯል

ከገጽ ፲፬ የዞረ

በላዩ ላይ የጌታና የ12ቱ ሐዋርያት ስዕል ተቀርጾበታል ። አሠራሩንና ቅርጹን የመረመሩ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ስዕሉ የተቀረጸው በ1ኛው ምዕት ዓመት ሳይሆን እንዳልቀረ ገምተዋል።አስደ ናቂነት ያለው ከሥዕሉ አሠራር ወይም ከቅርጹ ላይ አይደለም ይህ የሌላ ጽዋዕ መያዣ ማኅደር ነው ይህ ጽዋዕ በውስጡ የያዘው ሌላ ጽዋዕ አለ ዋናው ቁም ነገሩ ያለውም እዚህኛው ጽዋዕ ላይ ነው ። ይህ ጽዋዕ ጌታ በምሴተ ሐሙስ የሥጋ ወደሙ ሥርዓት በሠራበት ሰዓት ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ..." ብሎ ወይኑን ወደ አማናዊ ደሙ የለወጠበት ጽዋ ነው ። በሶርያ ሀገር ከአንጾኪያ ከተማ ፤ ከአንድ የካቴድራል ፍራሽ ውስጥ እ.ኤ. አ. በ1910 ዓ.ም. ሊገኝ ችሏል ።

ኢየሩሳሌም በ70 ዓ.. በሮማ ሠራዊት ስትወረር አንጾኪያ አካባቢው ለነበሩት አብያተ ክርስቲያናት እንደ መዲና ስለነበረች ይህን የተቀደሰ ክብርና ውድ ዕቃ ምዕመናን አሸሽተው አንጾኪያ ወዳለው ወደዚሁ ቤተ ክርስቲያን አምጥተውታል ። በዚያም በክብር ሲኖር ኋላ ቤተ ክርስቲያኑ ሲመዘበር ፤ በፍርስራሹ ውስጥ ተቀብሮ ቆይቶ እነሆ ባሁኑ ጊዜ ከተቀበረበት ተገኝቶ ሊወጣ ችሏል ። ዋናው ጽዋ እንደ ማሕደሩ ሁሉ ከንጹሕ ብር የተሠራ ነው ። ግን በላዩም ሆነ በውስጡ ቅርጽ ወይም ጽሕፈት የለበትም ። እሱም ዛሬ በኒውዮርክ ነዋሪ በሆኑት በሚስተር ፋሂም ካውጅክጂ ይገኛል ።



www.ethiopianorthodox.org

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር

በዚህ ዓምድ ለምናቀርባቸው ጥያቄዎች በየጊዜው ብዙ ሰዎች መሳተፋችሁን ስለምናይ በጣም ደስ ይለናል ። ለወደፊቱም ያለማቋረጥ እንደምትቀጥሉ ተስፋ እናደርጋለን ።

በየውድድሩ አሸናፊ ለሚሆኑ ሦስት ሰዎች ሽልማት የምንሰጥ ሲሆን ፤ በተጨማሪም ያለ ማቋረጥ በውድድሩ ለሚካፈሉ ሰዎች በዓመቱ መጨረሻ በየጊዜው ባሳዩት ውጤት መሠረት ሽልማት የምንሰጥ መሆኑን ስንገልጽ በደስታ ነው ።

የዚህ ወር ጥያቄዎቻችን እነሆ

1. እሥራኤላውያን እርሾ ያልገባበት ቂጣ እንዲበሉ ታዘው ነበር ፤ የታሪኩን መነሻ ፤ አደራረጉንና መንፈሳዊ ትርጉሙን ግለጽ ።
2. ጌታ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ፡-"እናንተ የምድር ጨው ናችሁ" ሲል ምን ማለቱ ነበር?
3. የመላእክት ቁጥር ስንት ነው?
4. እግዚአብሔር ሲጠራው ድምጹን መለየት የተሳነው ወጣት ማን ነበር?
5. እስራኤል ከምድረ ግብፅ ባርነት ነፃ ከወጡ በኋላ ናፈቁን ያሏቸው ምግቦች ምን ነበሩ?
6. ኢትዮጵያዊቱ የሙሴ ሚስት ስም ማን ነበር?
7. በብሉይ ኪዳን የተነገረለት ታዋቂ ሯጭ ማን ይባላል?

የጐደሉትን ቃላት ሙላ

8. አምላክህን ...............ተዘጋጅ ።
9. እናንተ .............ሸክማችሁ...... ............ወደ እኔ........አሳርፋችኋለሁ ።
10. ........በደጅ ቆሜ ........ማንም ............... .................ደጁንም .........................ወደ እርሱ እገባለሁ ።

ለያንዳንዱ ጥያቄ መልስ የሚገኝበትን መጽሐፍ ፤ ምዕራፍና ቁጥር ጥቀስ ። መልሱን እስከ ኅዳር 30 ቀን በሚከተለው አድራሻ ላኩልን፦

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር

የመ.ሣ.ቁጥር 1252
አዲስ አበባ

**የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር**

የፖ. ሣ. ቁጥር 1252
ስልክ 15 82 33
አዲስ አበባ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማል እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org